






# ፯



## ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ
## 1907 –
## ትንፋሽ ረጅም እግረ ብርቱ

በባዶ እግሬ በመሮጥና እነ አበበ ቢቂላን... ወደ ውድድሩ ዓለም በመሳብ፣ ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርት ፋና ወጊ ነኝ

«ለኢትዮጵያ ሕዝብና ለአገሬ በገባሁት ቃል ኪዳን መሠረት ሬሳዬ የሚወጣው ከሩጫው ሜዳ ነው» የሚሉት አትሌት ዋሚ የተወለዱት ጥር 11 ቀን 1907 ዓ.ም. ነው። የአቶ ቢራቱ በራቄ እና የወ/ሮ ወርቄ አያና ልጅ የሆኑት ዋሚ፤ የትውልድ ስፍራቸው ከአዲስ አበባ ከተማ በ21 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ በሚገኘው ሱሉልታ ወረዳ አካኮና መነ አብቹ በተባለው ቀበሌ ገበሬ ማኀበር ነው። ዋሚ የ6 ወንዶችና የ5ሴት ልጆች አባት፣ የ21 ልጆች አያትና የ11 ልጆች ቅድመ አያት ናቸው። በኢትዮጵያ የአትሌቲክስ ስፖርት ታሪክ ፈር - ቀዳጅ ከሆኑት መካከል አንዱ አትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በራቄ፣ ዛሬ በ93ኛ ዓመት ዕድሜአቸው መጀመሪያ ላይ ናቸው። እሑድ ጠዋት የካቲት 18 ቀን 1999 ዓ.ም. በጃንሜዳ በተካሄደው 24ኛው የአገር አቋራጭ ውድድር በህዋቂዎች ምድብ ከእነ ስለሺ ስህንና ታደሰ ቶላ እንዲሁም ከሌሎች አትሌቶች ጋር ተሰልፈው ሲሮጡ ታይተዋል።

የልጅነት ዘመን ትዝታቸው ከጊዜው መርዘም አኳያ እጅግ በጣም ሩቅና አውስተው የማይጨርሱት መሆኑን ቢናገሩም፣ «በአጭሩ እኔ በወጣትነትና በልጅነት ዘመኔ እኩዮቼንና የበላዮቼን ከ10 እና ከ12 ጊዜ በላይ በሩጫ ደርቤ ዐልፋቸው ነበር። ይህንን የልጅነቴን ዘመን ትውስታ እሑድ የካቲት 18 ቀን 1999 ዓ.ም. ጃንሜዳ ላይ በተካሄደው 24ኛው አገር አቋራጭ ውድድር ላይ መልስ ብዬ መመልከት ችያለሁ። እያለፉኝ ሲሄዱ የነበሩት ወጣቶች ያኔ በወጣትነት ዕድሜዬ የነበረኝን ጥንካሬና የአይበገሬነት ስሜት መልሰው አሳይተውኛል። ይህ አሁን በጃንሜዳ የሆነው የልጅነት ዘመን ትዝታዬ ተገላቢጦሽ ሆኖ አግኝቼዋለሁ» ይላሉ።

«ወላጆቼ ያሳደጉኝ በማርና በወተት፣ በጨጨብሳና በጩኮ ነው። ከእረኝነት ወደ ግብርናው ሙያ የተሸጋገርሁትም እንደ ሰንጋ ፈረስ እየተቀለብሁ ሲሆን የጐደለብኝ ነገር አልነበረም። ልጅ እያለሁ ሚዳቋ፣ ጥንቸል፣ ጃርትና ቆቅ እያባረርኩ አድን ነበር።' የሩጫን ጥበብ ከሯጭ ፍጥረታት ዱካ





የተማሩት ዋሚ ከፈረስ ጋር የተወራረድኩበትም ጊዜ ነበር ይሉናል። ሩጫን የጀመርሁት በእንዲህ ዓይነት ሁኔታ ነበር። በገና ጨዋታና በሌሎች የኦሮሞ ባህል ጨዋታዎች ከሱሉልታ እስከ ሰላሌ፣ ከሰላሌም እስከ ባሌ ድረስ የታወቅሁ ነበርሁ።»

«...አፍላ ወጣት ሳለሁ እናቴ ከገበያ ቡና ጠቅልላ ያመጣችበትን የጋዜጣ ቅዳጅ ተመለከትኩ። በቍራጩ የጋዜጣ ገጽ ላይ አንድ አጭር የሆነ ነጭ ሰው ሲሮጥ ይታያል። ያ ጋዜጣ ስለ ሰውዬው አሸናፊነትና ጥንካሬ የሚገልጽ ሐሳብ አስፍሯል። እሱን ከተመለከትሁ በኋላ እኔ ረዥሙም እና ጠንካራ ነኝ፤ ተራራ ዞሬ እሮጣለሁ፤ የመወዳደር ዕድል ባገኝ ይህንን ሰው አሸንፈዋለሁ የሚል ስሜት አደረብኝ። ይህንንም ስሜት ለአራት ዓመታት ያህል በአእምሮዬ ሳብላላው ቈየሁ።»

አትሌት ዋሚ፣ ወደ አትሌቲክሱ ስፖርት የመጡት መስከረም 5 ቀን 1945 ዓ.ም. ወደ ውትድርናው ዓለም ከገቡ በኋላ ነበር። በጊዜው በአሥመራ በሁለተኛ ክፍለ ጦር ሰራዊት አባልነት ተመድበው ሳሉ በከተማይቱ ነባርና አዲስ ቅጥር ወታደሮች መካከል በተካሔደው የሩጫ ውድድር ተሳታፊ ሆኑ። በውድድሩ ዋሚ አንደኛ ሲወጡ የእሳቸው አቻ ቅጥር የነበረው (ለውትድርና በአንድ ላይ የተቀጠሩ) ወታደር ሽጉጤ ቢሆንኝ ሁለተኛ ወጣ። በዚህ ዓይነት መንገድ የአትሌቲክሱን ሕይወት ጀመሩ። በአገር ውስጥ የማራቶን ውድድር ሲኖር የሚቀናቀናቸው ጠፋ።

«በባዶ እግሬ በመሮጥና እነ አበበ ቢቂላን... ወደ ውድድሩ ዓለም በመሳብ፣ለኢትዮጵያ አትሌቲክስ ስፖርት ፋና ወጊ ነኝ» የሚሉት ዋሚ ቢራቱ በ 1953 ዓ.ም. ጃፓን ቶኪዮ ላይ በተካሄደው ዓለም ዐቀፍ የማራቶን ውድድር ሻምበል አበበ ቢቂላን ተከትለው ሁለተኛ ወጥተዋል። ኢትዮጵያን በመወከል በምሥራቅ አፍሪካ፣ በጃፓን፣ በቼኮዝሎቫኪያና በቀድሞዋ ሶቭየት ኅብረት ተገኝተው በመወዳደር አመርቂ ውጤት አስመዝግበዋል። በተለያዩ የውድድር ዘርፎች



ማለትም በ1,500፣ በ3,000፣ በ5 እና በ10ሺህ ሜትር፣ በ21፣ በ25 እና በ32 ኪ.ሜ. አገር አቋራጭ ሩጫና በማራቶን ተሳትፎ አድርገዋል። ዋሚ አገራቸው ኢትዮጵያ በዓለም ዐቀፍ መድረክ ስሟ በክብር እንዲጠራና ሰንደቅ-ዓላማዋም ከፍ ብሎ እንዲውለበለብ በማድረግ በኩል ላበረከቱት ቀዳማይ አስተዋፅኦ በሰሜን አሜሪካ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን መካከል በየዓመቱ በሚካሄደው የኢትዮጵያውያን የእግር ኳስ ውድድር ላይ በ1994 ዓ.ም. በክብር እንግድነት እንዲገኙ ተደርገዋል።

ዋሚ በአገር፣ በአህጉርና በዓለም ዐቀፍ ደረጃ በተካሄዱ ውድድሮች 51 የወርቅ፣ 44 የብርና 30 የነሀስ ሜዳሊያዎችን ለመሸለም የበቁ አትሌት ናቸው። ዋሚ ቢራቱ «በሮም ኦሎምፒክ ተሳታፊ መሆን ብችል ኖሮ ቢያንስ የሁለት ወርቅ ሜዳሊያዎች ባለቤት ልሆን እችል እንደነበር አልጠራጠርም» ይላሉ። «ሆኖም ግን ከውድድሩ ስድስት ቀናት በፊት በሰውነቴ ላይ በ19 ቦታዎች ብጉንጅ[1] ወጣ። በዚህም ምክንያት ወደ ሮም ሳልሄድ ቀረሁ። እኔ ብቻ ሳልሆን አሠልጣኞቼ በ5 ሺ. እና በ10ሺህ እንደዚሁም በማራቶን አሸናፊ መሆን እንደምችል፣ በወቅቱ በዓለም ዐቀፍ ደረጃ አሉ የሚባሉ ሯጮች የነበራቸውን ዝቅተኛ ሰዓት ግምት ውስጥ በማስገባት ተስፋ ጥለውብኝ ነበር» በማለት በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ይገልጻሉ።

ዋሚ ነባሩንና የአሁኑን የአትሌቲክስ ስፖርት ገጽታ ሲያስተያዩም «ለምሳሌ በእኛ ጊዜ ሰዓት የሚመዘገብበት ሁኔታ አልነበረም። ቀድሞ የገባ ያሸንፋል። እንደ ዛሬው በአንድ የውድድር ዓይነት ብቻ ተወዳደሩ አይባልም። አቅሙ የቻለ በማራቶን፣ በ10ሺ.፣ በ5ሺ. እና በ3ሺህ ሜትር መወዳደር ይችላል። አሁን ስፖርታዊ ትጥቆችን እንደ ልብ ማግኘት ይቻላል። ያኔ ግን ችግር ነበር። እኛ ፈጣንና ጉልበት ያለን ሯጮች በነበርንበት ዘመን ምግብ የምናገኘው የፈለግነውን ያህል ነበር። ክትፎ የምንበላው በ15 ሣንቲም፤ ቀጥሎም በ25 ሣንቲም ነበር።



[1] ብጉንጅ በቆዳ ሥር በስሱ በሰውነት የተለያየ ሥፍራ እያበጠ እንደ ብጉር የሚወጣና የሚያላውስ ህመም ነው



የመጨረሻው የክትፎ ዋጋ በትልቁ ጣባ 50 ሣንቲም መሆኑን አልዘነጋውም። የቻለ ሰው ሁለት ወይም ሦስት ጣባ ክትፎ ይሰለቅጣል። እንደዚያ በልተን፣ በልብሳችን ውስጥ አሸዋና ድንጋይ አድርገን ሜዳ ፣ ጋራና ኮረብታውን እያቋረጥን ልምምድ እናደርግ ነበር። በውድድር ጊዜም እንደ ነፋስ ሽው ብለን በመሄድ እናሸንፋለን። በአሁኑ ጊዜ ድኻ የሆነ ሰው ሩጫ ሮጦ የፈለገውን ምግብ መብላት አይችልም...» በማለት በእርሳቸው ጊዜ የነበረውንና በዚህኛው ዘመን ያለውን የአትሌቲክስ ስፖርት ሁኔታ ያነጻጽራሉ። ዋሚ የልጆቻቸውን እናት ወ/ሮ ድባቤ በዳዳን ባገቡበት ጊዜ የነበረውን የሠርግ ሥነ-ሥርዓት እንዴት እንደነበረ ሲያስረዱ «ማን እውነት መሆኑን ያምናል? እንደ ዛሬ በፊልም ተቀርጾ የሚታይ ነገር በሌለበት ሁኔታ ... » የሚለውን ቃል በማስቀደም « በ60 ፈረስ ታጅቤ ነበር። በእግሩ የነበረው ሰው ቁጥር አይታወቅም። አባቴ የደገሰው ድግስ፣ የተጣለው ሠንጋ፣ ሁለት ወር ሙሉ ተበልቷል። የሠርጌ ቀን ልዩ ነበር ... » ብለዋል።

ዛሬም ድረስ የሚወዱት ምግብ ጨጨብሳ፣ ጩኮ፣ ዕንቍላል፣ ወተትና ማር መሆኑን ይናገራሉ፤ «በጦር ሜዳና በሌላ ሙያዊ ዘርፍ ሳይሆን በስፖርቱ ዓለም የኢትዮጵያ ባለውለታ ነኝ። ከእኔ ቀጥሎ ደግሞ አበበ ቢቂላና ማሞ ወልዴ ናቸው።» በማለት ወደ ቀጣዩ ትረካቸው ያልፋሉ። ሦስት መሠረታዊ የሚሏቸውን ምክንያቶች በማስቀደም የኢትዮጵያ ባለ ውለታ አገር ብለው የሚያስቡትን አገር ይጠቍማሉ፡-

1ኛ- እኔ ለመጀመሪያ ጊዜ በማራቶን ያልተወዳደርሁበትን ምክንያት በዓለም ደረጃ በማሳወቃቸው 2ኛ- በታኅሣሥ 1953 ግርግር ማግስት በአገራችሁ 1ኛ የሆነውን አትሌት ከአበበ ቢቂላ ጋር ወደ ቶኪዮ እንድትልኩ ሲሉ ለጃንሆይ በጻፉት ደብዳቤ መሠረት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ በዓለም አቀፍ መድረክ በማራቶን ውድድር የመሳተፍ ዕድል ላገኝ በመቻሌ፤ 3ኛ- በእኔ እና በሻምበል አበበ ቢቂላ ስም፣ ዘመናዊ የእስፖርት ትጥቅ ለመጀመሪያ



ጊዜ የክብር ዘበኛ ስፖርት ክለብ እንዲያገኝ በማድረጋቸው የኢትዮጵያ ባለውለታ ሀገር የሆነችው ጃፓን ናት ይላሉ።

ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ በጃፓን ቶኪዮ ማራቶን ተሳትፎ አድርገው ከአበበ ቢቂላ በመቀጠል 2ኛ ሲወጡ ያጋጠማቸው ሁኔታ በግላዊ የሕይወት ታሪካቸው ውስጥ ጉልሕ ሥፍራ አለው። 42 ኪ.ሜ. ከ190 ሜትር ይሸፍን የነበረውን ርቀት እስከ 40ኛው ኪ.ሜ. ድረስ ሲመሩ ቆዩ። ነገር ግን ከነበረው ሙቀት የተነሣ እግራቸው መላላጥ ጀመረ። የሚሮጡት ባዶ እግራቸውን ነበርና ይፈስ የነበረው ደም የሚሮጡበትን መንገድ አቀለመው። ሆኖም መሮጣቸውን ቀጠሉ፤ አበበን አሳልፈው ሁለተኛ ወጡ። በመላላጥ ለተጐዳው እግራቸውም የጃፓን ሐኪሞች ወደ ሆስፒታል ወስደው የሕክምና ርዳታ አደረጉላቸው። ይህንን የተመለከቱ የአገሪቱ ጋዜጠኞችም፣ «የኢትዮጵያዊው አትሌት የዋሚ ቢራቱ እግር የሰው አይደለም» ብለው ጻፉ። ይህም ከረጅም ዓመታት በፊት ገጥሟቸው ለነበረውና እሳቸውም ለሰጡት ምላሽ ሌላ ትውስታን ይጭራል፦ እኒህ ፋና ወጊ አትሌት በእግራቸው ሲኳዙ፣ ጎረቤታቸው የሆኑት ኮሎኔል ተክለ ወ/ሚካኤል ያገኟቸውና፣ «ዋሚ ና በመኪና ልሸኝህ...» ቢሏቸው፣ «የለም እቸኩላለሁ፤ ከእርስዎ ኮሣሣ መኪና ይልቅ የእኔ እግር ይሻላል ...» በማለት የሰጡት ምላሽ እስከ ዛሬም ድረስ የሚወሳ የታሪካቸው አካል ሆኗል።

መጋቢት 1996 ዓ.ም. «አትሌቲክስና ዋሚ ቢራቱ ለግማሽ ምእት ዓመት» በሚል ርእስ የፎቶ ኤግዚቢሽን ያዘጋጀው የአትሌቱ 10ኛ ልጅ ጃገማ ዋሚ፣ «የአባቴ አንፀባራቂ ታሪክ በሰለጠነው ዓለም ተከናውኖ ቢሆን ኖሮ በጊነስ ቡክ ላይ ሊጻፍ ይችል ነበር። አትሌት ዋሚ ከ1500 ሜትር እስከ ማራቶን ባለው የውድድር ዘርፍ ተሳታፊና አመርቂ ውጤት ያስመዘገቡ መሆናቸውን፣ በአሠልጣኝነትና በወጌሻነት ማገልገላቸውን፣ ለ50 ዓመታት ከመሮጥ ያልቦዘኑ መሆናቸውን የማያውቁና ይህንንም ሐቅ የፎቶው ኤግዚቢሽን በተዘጋጀበት ጊዜ የተረዱ ኢትዮጵያውያን፣ ለአባቴ ያላቸውን ከፍተኛ አድናቆት ገልጸዋል። እሱ ከአበበ







ቢቂላና ከማሞ ወልዴ ጀምሮ እነ ደረጄ ነዲን፣ ለማ ገዳን፣ ከበደ ባልቻንና ሌሎችንም አትሌቶች ኢትዮጵያ እንድታፈራ መሠረቱን ጥሏል። የበኩሉንም የአርአያነትና የአሠልጣኝነት ድርሻ ተወጥቷል» ብሏል። በተጨማሪም የአባቱን ጽናት፣ ትዕግሥትና ተስፋ-አይቈርጤነት ለብዙዎች ትምህርት ሰጪ እንደ ሆነ አስገንዝቧል። በ70ዎቹ ዕድሜ ላይ ሆነው 42 ኪሎ ሜትርን ሮጦ መጨረሱ በዓላማቸው የማይወላውሉ መሆናቸውን ያሳያል ሲልም አስተያየቱን ሰጥቷል።

«ዋሚ ቢራቱ በአካልም ሆነ በመንፈስ ጠንካራ ሰው ናቸው። እንደ እርሳቸው ዓይነት ለእግዚአብሔር ሰላምታ የሚፈጥንና ሕሙማንን ለመጐብኘት የሚተጋ ሰው አላጋጠመኝም» የሚለው ደግሞ የ32 ዓመቱ ወጣት አብዱልቃድር ደሊል ነው። አትሌት ዋሚን እንደ ጎረቤትነቱ በቅርብ እየተመለከተ ያደገውና በተግባራቸው ሁሉ በእጅጉ የሚደነቀው አብዱልቃድር፣ «ሀብታም ድኻ፣ ትንሽ ትልቅ ሳይሉ ጨዋነትና ትሕትና በተሞላበት ሁኔታ የሚያቀርቡት ሰላምታ አርዓያነቱ የጐላ ነው። ከሠፈራቸው ሰዎች መካከል አንዱ ስብራት ወይም ወለምታ ሲያጋጥመው ወደ ታማሚው ቤት ድረስ በመሄድ የወጌሻነት ሕክምና ይሰጣሉ። ለአገልግሎታቸውም ምንም ክፍያ ሳይቀበሉ በሙያቸው ሰዎችን ይረዳሉ። ዳሩ ግን እኒህ ትሑት፣ ሰላምተኛ፣ የሰውን ልጅ በእኩልነት አክባሪና በአትሌቲክስ ዓለም ጀግንነታቸውን ያስመሰከሩ ሰው፣ አንድ ለታሪክና ለመጪው ትውልድ ማስተማሪያ መሆን የሚችል ዶክመንተሪ ፊልም ያልተሠራላቸው መሆኑ ያሳዝናል...» በማለት የበኩሉን ሐሳብ ሰንዝሯል።

አትሌቱ የሚቈጩበት፣ የሚያዝኑበትና «የዕድል ጕዳይ ነው» የሚሉት፣ እንዲሁም በጣም የሚከፉበት ትውስታ አላቸው። ጳጕሜ 2 ቀን1995 ዓ. ም. ፣ መስከረም 17 ቀን 1996፣ የካቲት 28 ቀን 1996 ዓ.ም. እና በሌሎችም ቅርብ ጊዜያት የ6፣ የ10፣ የ12 ኪ.ሜ. ሩጫ ከመወዳደራቸውም ባሻገር፣ በተለይም በመስከረም 1996 ቱሪዝም ኮሚሽን



ባዘጋጀው ውድድር የ21 ኪ.ሜትሩን ርቀት በ2 ሰዓት ከ0.5 ደቂቃ በመፈጸም የተለየ አድናቆትን ያተረፉ አንጋፋ አትሌት ናቸው። የአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ታሪክ እጅግ ረዥም፣ ሰፊና ጥልቅ ነው። በርግጥም የዘጠና ሦስት ዓመት የዕድሜ ባለ ጸጋ ለ54 ዓመታት ከስፖርት ሜዳ ያልጠፉ ሰው የሕይወት ዘመን ትረካ በአጭር ሊቋጭ የሚችል አይደለም። ሆኖም ደማቁ ዋሚ በቀጣይ የኢትዮጵያ አትሌቲክስ ታሪክ ሲወሱ ይኖራሉ። ይሄ ነው «እድሜ ይስጥልኝ» ማለት!

## መወድስ

**ፈር ቀዳጅ አትሌት ዋሚ ቢራቱ**
**ቁመተ ሎጋ ትንፋሽ ብርቱ**
**ዐሥር ጊዜ ዐሥር ዓመት ተቆጥሮ**
**ዋሚ ይሮጣል ትንፋሹን ቋጥሮ**

## ትምህርተ ውልብታ

**ጽናት የዋሚ ሕይወት ዓይነተኛ ምልክት ነው**

**ተፈጥሮና አካባቢ የለገሳቸውን ማንነት ጊዜአቸው ከሚፈቅደው ሆኔታ ጋር በማቻቻል የአንድ ሙያ ባለቤት መሆናቸው፤**

**የሩጫ ስፖርትን ለድል ብቻ ሳይሆን ለስፖርቱ ፍቅር መግለጫ እስከመጨረሻው የጸኑበት መሆናቸው፤**





## የውልብታ ምንጮች

ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ የካቲት 1999 ዓ.ም.

ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ ልጅ ከአቶ ጃገማ ዋሚ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ የካቲት 1999 ዓ.ም.

ከአትሌት ሻለቃ ባሻ ዋሚ ቢራቱ የጐረቤት ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ

በእንግሊዝኛ ቋንቋ ስለ አትሌቱ የተጻፈ አጭር የሕይወት ታሪክ...

በአማርኛ የተዘጋጀ የዋሚ ቢራቱን ማንነት ጠቋሚ አጭር ትረካ





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ






## ፯



**ይድነቃቸው ተሰማ**
**1914–1979**
**የአፍሪካ እግር ኳስ አባት**

*የኢትዮጵያ ስፖርት ተዳክሞ ከማይ ሞቴን እመርጣለሁ*

«ለመታሰቢያ ነው እግዜር የሠራቸው
በሰማይ ኤልያስ በምድር ይድነቃቸው»

ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ

ከብሩህ ገጽታቸው ጋር ስምሙ ሆኖ የተሠራ የሚመስል ውሃ መልክ መነጽር ከቶ አይለያቸውም። ሞላ ባለ ትክለ ሰውነት በቢሮ ጎላፊዎች አለባበስ ይታያሉ፤ እንዲህ ሲያዩአቸውም የወጣትነት ዘመናቸውን የማያውቁ በርካታ ሰዎች ከስፖርት ደጋፊነት ወደ ስፖርት አስተዳደር የመጡ እንደሆኑ ይገምታሉ። እርሳቸው ግን ኳሷን፣ ድቡልቡሏን እያንከባለሉ በዘጠና ደቂቃ ሩጫዎች ከመንደር እስከ ዓለም ሁተፍ ደረጃ በበርካታ የእግር ኳስ ሜዳዎች ላይ በእግራቸው መዳፍ የፈረሙባቸው ሰው ናቸው።

ዘመኑ የፖለቲካ መረጋጋት የሰፈነበት አልነበረም፤ በአፄ ምኒልክና በልጅ ኢያሱ የንግሥ ሽግግር ወቅት በዙፋኑ ዙሪያ የሥልጣን ጉምዝርታ የኃይል ውጥረት ነበረ። በሂደቱም የዚህ ፖለቲካ ፍትጊያ ዳፋ ደርሷቸው በልጅ ኢያሱ ደጋፊነት ተወንጅለው ጅማ ግዞት ከተጋዙት መካከል አንዱ የፈርጀ ብዙ ዕውቀት ባለቤት የነበሩት ነጋድራስ ተሰማ እሸቴ አንዱ ናቸው። ነጋድራስ በግዞት አንገታቸውን ባጐነበሱበት የትካዜ ጉም ውስጥ ሆነው የኢትዮጵያንና የአፍሪካን ስፖርት ከወደቀበት ቀና ሊያደርግና አድጎ የስፖርት አባት ሊሆን ይድነቃቸው ተሰማን ወለዱልን። ይህ የሆነው በዕለተ እንቁጣጣሽ 1914 መባቻ ላይ ነው። ነጋድራስ ግዞታቸው ተነሥቶ በምሕረት አዲስ አበባ ሲመጡ የአራት አመት ልጅ የነበሩት ይድነቃቸው አህጉራዊ የሕይወት ጥሪአቸውን ይወጡ ዘንድ ማደጊያቸው አራዳ ሆነ።



በጅምሩ ዕድሜአቸው ጉልበተኛና አፍቃሬ ስፖርት ሆኑ፤ ትንፋሻቸውንና አካላቸውን ባዳበሩበት የተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ሜዳ በእግር ኳስና በአትሌቲክስ ስፖርት የፊተኛው መሥመር ባለ ዕጣ ሆኑ። በጊዜው የተከሠተው የኢጣሊያ ወረራም የኳስ ዕጣቸውን



አልነጠቃቸውም ነበር። ከአራዳ ቡድን ጋር አርመኖችን ይጋጠሙ ጀመር። በዚያን ጊዜ በሜዳው ከሚራወጡት ተጫዋቾች ሁሉ ጐልቶ ይታይ የነበረ ባለ 11 ቍጥር መለያ ለባሽ ቅጽል ስሙ «ቦንዳሳ» የተባለው ተጫዋች ነበር። የበርካታ ሰዎች ሀይን ያረፈበትና ጆሮ የሳበው ይህ ሰው የኳሱ ሜዳ የጠዋቱ ጀግና ይድነቃቸው ተሰማ ነበር። ፋሺስታዊው የቅኝ አገዛዝ ደመና በኢትዮጵያ መሬት ላይ ሳይዘንብ በዐርበኞች ትግል በተገኘው የነፃነት ነፋስ በነነ፤ ይድነቃቸውም ከሚያስደንቅ የኳስ ክህሎት ጋር ወደ ኢትዮጵያ የስፖርት ትእይንት በመጠጋት የበለጠ እየጐሉ መጡ።

ገና የ14 ዓመት አዳጊ ወጣት እያሉ በ1935 ዓ.ም. በአገራችን የመጀመሪያው የስፖርት ክለብ የሆነው የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድን ሲቋቋም ጋሽ ይድነቃቸውም ለቀሪው ድንቅ የሕይወታቸው ጥሪ መነጠሪያ ይሆን ዘንድ ወደዚህ ቡድን ገቡ። ይህም ድልድይ ሆኗቸው ለኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድን ለመመረጥ በቁ። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የኳሱ ፍቅር የጠናባቸው ይድነቃቸው ሥራቸው ኳስ፣ ዕረፍታቸው ኳስ፣ ሽርሽራቸው ኳስ፣ ቀጠሯቸው ሁሉ ኳስ ሜዳ ሆነ። የይድነቃቸው ክለባዊና አገራዊ የድርሻ ምዕራፎቻቸው የሚነበቡት 23 የእግር ኳስ ጨዋታ ዓመታትን ባሳለፉበት በዚሁ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድንና ከ1948 ዓ.ም. እስከ 1954 ለ 15 ጊዜያት በተሰለፉበት የብሔራዊ ቡድን ውስጥ ነው። ነገር ግን ከሌሎች ተለይተው በመውጣት ታላቅ አገራዊና አህጉራዊ የስፖርት ዓለም አስተዋፅኦአቸው የሚጀምረው ከእንዲህ ዓይነቱ የኳስ ተጫዋችነታቸው ምዕራፍ በኋላ ነው።

ይድነቃቸው የብራዚልን የእግር ኳስ ቡድን መውደድ ብቻ ሳይሆን፣ ለረጅም ዓመታት ለተጫዋቱባቸው የጊዮርጊስና የብሔራዊ ቡድኖችም ምሳሌ እንዲሆን የጠበቀ ምኞት ነበራቸው። ከዚህም የተነሣ በአሠልጣኝነታቸው ጊዜ የኢትዮጵያን ቡድን የጨዋታ ዘይቤ ወደዚያ ማራኪ ቡድን ዘይቤ ቀየሩት። እንደ መታያ ውጤትም በይድነቃቸው ተሰማ መሪነት ኢትዮጵያውያን እስከ ዛሬ ድረስ በብቸኝነት



የሚጠቅሱት፣ በአዲስ አበባ ተደርጎ የነበረው የ1962ቱ የሦስተኛው የአፍሪካ ዋንጫ ባለ ድል ለመሆን በቃን። በዚህ ድል ምክንያትም የተነሣ 1960ዎቹ ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ጨዋታ ወርቃማ ዓመታት ተብለው ሊጠቀሱ ይችላሉ። ይህ ዘመን ኢትዮጵያ የአፍሪካን ዋንጫ የወሰደችበት፣ በመሥራችነትና በኀያል ቡድንነት የምትጠቀስበት፣ የቅዱስ ጊዮርጊስ ቡድንም የአገሪቱ ኃያል ቡድን ወደ መሆን የተሸጋገረበት፣ ስፖርታዊ ንቃትም ይበልጥ የዳበረበት ዘመን ነበር። ለዚህ ዘመን ስፖርታዊ ድምቀት ከሌሎች አጋሮቻቸው ጋር በመሆን በግንባር ቀደምትነት የሚጠቀሱት ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው። በወቅቱ በቅዱስ ጊዮርጊስና በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቡድኖች ውስጥ ተጨዋች ሆነው ከተሰለፉት ታላላቅ ሰዎች የምንሰማው ምስክርነት ለዚህ ሁሉ አስረጅ ይሆነናል፤ «ይድነቃቸው ተሰማ ስኬታቸው በተጫዋችነት እና በአሠልጣኝነት ላይ ብቻ አልነበረም። በተግባቢነታቸውና የተጨዋቾችን ሥነ ልቦና ፈጥኖ በመረዳት ችሎታቸው የተዋጣላቸው የቡድን መሪም ነበሩ። በቡድን ውስጥ ሰላማዊ አየር እንዲኖርና የእያንዳንዱ አባል በራስ የመተማመን ችሎታ እንዲያድግ በማድረግ ሰውየው ምን ጊዜም ለማይዘነጋ ውጤታማነት በቅተዋል።

ለኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን መሠረት የጣለውን የመጀመሪያውን የስፖርት ጉዳዮች ቢሮ በ1943 እ.ኤ.አ. የከፈቱ ሲሆን ለፌደሬሽኑ ሕግ እና ደንብ ከማርቀቅ አንስቶ፣ ዳኞችን፣ አሠልጣኞችንና የአስተዳደር አካላትን እስከ ማሠልጠን ድረስ ያለው ሓላፊነት ሁሉ እኒህ ታታሪ ሰው ትከሻ ላይ ያረፈ ነበር። ከኃላፊነታቸውም ጋር የተያያዙ የተለያዩ ችግሮች ተጋረጡባቸው። በአንድ ወቅት በየካቲት መጽሔት ላይ በተጻፈ የሕይወት ታሪካቸው ላይ ይድነቃቸው የአፍሪካን ብሎም የኢትዮጵያን ስፖርት ለማሳደግ ደፋ ቀና ሲሉ ነገሮች ሁሉ ቀላል ሆነውላቸው እንዳልነበር ተናግሯል። በ1953 ዓ.ም. አካባቢ የይድነቃቸውን እንቅስቃሴ ካልወደዱ ሰዎች መካከል ጥይት ተተኩሶባቸው እንደነበረ ይነገራል። ይህ አዝማሚያ ሥጋት ያሳደረባቸው ቤተ ዘመዶቻቸው ሥራውን እንዲተው





ሊያግባቧቸው ሲሞክሩ፣ «እኔ ሥራዬን ለቅቄ እዚህ ያደረስኩት የኢትዮጵያ ስፖርት ተዳክሞ ከማይ ሞቴን እመርጣለሁ» በማለት በአቋማቸው እንደ ጸኑ ተናግሯል።

ለኢትዮጵያ ዘመናዊ ስፖርት አባት ተብለው የሚታወቁት ይድነቃቸው ተሰማ ለአፍሪካ እግር ኳስም አባት ናቸው። የአፍሪካ አገሮች በተለይም መሥራች የሆኑት ኢትዮጵያ፣ ግብጽና ሱዳን የአፍሪካን እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን ሲያቋቁሙ ይድነቃቸው ተሰማ ከዚያ ታሪካዊ ቀን በስተ ጀርባ ነበሩ። ኢትዮጵያ በኮንፌዴሬሽኑ ለአፍሪካ እግር ኳስ እድገት ስትታገልና የአፍሪካውያን ተጫዋቾች ሕልም እንዲሳካ ለማድረግ ስትጥር በካፍ የተለያዩ የኀላፊነት ቦታዎች ላይ የነበሩት እሁንም ይድነቃቸው ተሰማ ናቸው። በአጠቃላይ ኢትዮጵያዊው የማይታክቱ ሰው በአፍሪካ ምድር ያልገኙበት ቦታ የለም። አቶ ፈቃደ ማሞ መጋቢት 28 ቀን 1999 ዓ.ም. ታትሞ በወጣው ኢትዮ ስፖርት ጋዜጣ ስለ ኢትዮጵያ እግር ኳስ ነባርና ወቅታዊ ገጽታዎች በሰጡት ትንተና የመግቢያ ሐተታቸው ላይ፣ በአንድ ገጠመኝ የተመለከቱትን የአፍሪካ አገሮች ለይድነቃቸው ተሰማ ያደርጉላቸው የነበረውን አቀባበል ከንጉሣዊ አቀባበል ጋር ያስተካከሉት ሲሆን «አቶ ይድነቃቸው ይህን ያህል ክብር ያገኙት ለአፍሪካ እግር ኳስ በፈጸሙት እኩሪ ተግባርና ባላቸው ዕውቀት ጭምር ነው። በእኒህ ትልቅ ሰው ምክንያት ኢትዮጵያችን በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን የነበራት ተሰሚነት ከፍተኛ ነበር» በማለት የይድነቃቸውን ጉልሕ አሀጉራዊ ተሳትፎ ያስታውሳሉ።

በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ከ1957 እስከ 1987 ዓ.ም. በተለያዩ የኀላፊነት ቦታዎች በሠሩበት ወቅት የአፍሪካ ዋንጫን ለማሳደግና አፍሪካ በዓለም የእግር ኳስ መድረክ ላይ ያላት ተቀባይነትም ሆነ ተሳትፎ እንዲጨምር ከፍ ያለና መሪ ድርሻ ነበራቸው። ስፖርት የሰላም፣ የወዳጅነትና የጤንነት መድረክ በመሆኑ፣ የሲጋራ እና የመጠጥ ማስታወቂያዎች በእግር ኳስ መድረክ ላይ መታየት የለባቸውም



በማለት ለስፖርታዊ ሥነ ምግባር በጽናት የታገሉ ኢትዮጵያዊው የካፍ ፕሬዚዳንት ይድነቃቸው ተሰማ ነበሩ። ከዚህ የተነሣም ከተለያዩ የንግድ ኩባንያዎች ጋር ተጋጭተዋል። በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን አመራራቸው ጣሊያንኛ፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዝኛ ቋንቋዎችን አቀላጥፈው መናገራቸውም የአፍሪካን አገሮች በካፍ ጥላ ሥር በአንድነት ለማስተባበር ከፍተኛ ዕገዛ አድርጎላቸዋል።

የይድነቃቸው በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን Confederation Africaine de Football (CAF) የአመራር ኀላፊነት፣ ጨቋኝ ፖለቲካዊ ርዕዮተ ዓለምንም የመፋለም ተግዳሮት ገጥሞት ነበር። በነበሩባቸው የኀላፊነት ዓመታት ውስጥ አፍሪካ ገና ከቅኝ ግዛት ለማገገም የምትጥርባቸው ዓመታት ስለ ነበሩ በስፖርቱ ላይም በአህጉሪቱ ላይ ከዘረኝነት ጋር በተያያዘ ከፍተኛ ችግሮች ይደርሱ ነበር። ይህንንም በካፍ መርሖዎች በጽናት የታገሉ ሰው ናቸው።

ለአብነት ያህልም በሜክሲኮ የዓለም ዋንጫ ላይ የእንግሊዝንና የአርጀንቲናን ጨዋታ የዳኙት ቱኒዚያዊ ዳኛ የማራዶናን በእጅ የገባች ጎል በማጽደቃቸው ሊላው ዓለም አፍሪካዊው ዳኛ ላይ ጣቱን ቀሰረ። ከአውሮፓውያን የመሥመር ዳኞች ተነጥለው አፍሪካዊው የመሀል ዳኛ መብጠልጠሉ ያልተዋጠላቸው የወቅቱ የካፍ ፕሬዝደንት ይድነቃቸው ተሰማም፣ ዳኛው ከዚያ ጨዋታ በፊት ያሳዩትን ብቃት በመተንተን፣ ዳኛው የተሳሳቱት አፍሪካዊ ስለ ሆኑ አለመሆኑን በማስረገጥ ተከራከሩ። በተለያዩ ክስተቶች ላይም አፍሪካ ሌሎች የጨለማ አህጉር ብለው እንደሚያስቧት ሳትሆን፣ በዓለም ላይ በስፖርቱም ሆነ በሌላው መስክ መፎካከር የምትችል የብርሃን ምድር መሆኗን ሳይታክቱ አስረዱ።



የአፍሪካ እግር ኳስ ከስፖንሰሮች (የገንዘብ ደጋፊዎች) በሚገኘው ገቢ እንዲያድግም ከፍተኛ ጥረት ያደርጉ ነበር። በዋናነት ግን አቶ



ይድነቃቸው የንግድ ድርጅቶች በስፖንሰርነት ሰበብ የኮንፌደሬሽኑን ሕጎችንና ደንቦችን እንዳይጣሱ ታግለዋል። ከአቶ ይድነቃቸው ተሰማ አመራር በፊት የአፍሪካ አገራሮች የዓለም ዋንጫ ተሳትፎ በጣም ውሱን ነበር። 54 አገሮች ያሏት አፍሪካ በዓለም አቀፍ መድረክ ያላት የተሳትፎ ኮታ ማደግ እንዳለበት በተደጋጋሚ በመግለጽ ለአህጉሪቱ የድርሻ መብት ተከራክረዋል። እንዲህ ዐይነቱ ትግላቸውም ዘላቂ ውጤት በማምጣቱ ዛሬ የአፍሪካ የዓለም ዋንጫ ተሳትፎ ወደ አምስት አገሮች አድጓል።

ይድነቃቸው ተሰማ በፕሮፌሽናሊዝም ላይ ከብዙ ሰዎች ጋር የማያግባባ አቋም እንደ ነበራቸው ይነገራል። «የአፍሪካ ያላደገ ኢኮኖሚ ፕሮፌሽናሊዝምን ተሸክሞ የመጓዝ አቅም የለውም» ይሉ ነበር። የተጨዋቾች በፕሮፌሽናሊዝም መርሕ ወደ ተለያዩ የአውሮፓ አገሮች መድረክ መትመምም ባርነትን የመሳሰሉ ችግሮችን ያስፋፋል በማለት ተቃውመዋል። በዚህ ነጥብ ላይ በርካታ ሰዎችና በተለይም የስፖርቱ መሪዎች ከይድነቃቸው ተሰማ በተቃራኒ ጎን ቆመዋል።

በኦሎምፒክ ውድድሮች ላይ አፍሪካ በእግር ኳስ ስፖርት በአደጉ አህጉሮች በፕሮፌሽናሊዝም ስም እንዳትጎዳ ጥረት አድርገዋል። ይህንንም ለመተግበር በኦሎምፒክ የሚደረገው የእግር ኳስ ውድድር የወጣቶች መድረክ እንዲሆንና ከእንጋፋ ተጫዋቾች ከሦስት በላይ እንዳይሰለፉም ታግለዋል። ከፍተኛ ትግል ያደረጉበት ሐሳብ ተቀባይነት አግኝቶ አፍሪካ በኦሎምፒክ ሻምፒዮን በሆነችባቸው ጊዜያት ላይ ተንጸባርቋል።

ከይድነቃቸው የስፖርት ፍልስፍና እጅግ ሊጠቀስላቸው የሚገባ ሐሳብ በስፖርተኛ ምሉዕነት ላይ የሰጡት አስተያየት ነው። ለእርሳቸው የታላቅ አንጎል ባለቤት የሆነ ባለ ደቃቃ ሰውነት ምሁር ወይም የፈረጠመ ጡንቻ ያለው ባለ ደካማ አንጎል ስፖርተኛ ተቀባይነት ያለው አይደለም ፦



ባሬ የሰው ዘር ባደረገው ከፍተኛ ርምጃ ፊጠሩን ለአንጎል የተልበት ሥራን ለመኪና በሚያደላድልበት ጊዜ የሰው አካል እየተረሳ ሊሔድ ስለማይገባ አካልን በስፖርታዊ እንቅስቃሴ መገንባትና መጠበቅ ዕውቀትና ጤንቻ አብረው ማደግና አብረው በጤና መኖር እንዳለባቸው ተረጋግጧል።

የይድነቃቸው ሁለ ገብ የስፖርት አስተያየትና ሒስ በአፍሪካውያን ዘንድ ተደጋግሞ የታየውን ጎጂ እምነትንም ሁሉ ይዳስስ ነበር። በተለይ በአፍሪካ ስፖርት የጥንቆላ እምነትን በተመለከተ ይድነቃቸው ተሰማ እጅግ ጠንካራ አስተያየት ሰጥተው ነበር ፦

> ዛሬ በብዙ የአፍሪካ አገሮች የስፖርት ክለቦችን የሰው ኃይል ስንመለከት፣ ከአሠልጣኙ ጎን ደመወዝ የሚከፈለው አንድ «ጠንቋይ» እናገኛለን። በውድድር ጊዜ ግቡ እንጨት ላይ ዱቄት የሚነሰንስ፣ መረቡ ውስጥ ክታብ የሚቀብር፣ በዚህም የተነሳ ሽብርና አመጽ የሚፈጥር «ደጋሚ» አዘውትሮ ይታያል። ይህ እጅግ በጣም ኋላ ቀርና ኢ-ሳይንሳዊ ከሆነ አመለካከት የሚመነጭ አጉል ድርጊት ስለ ሆነ መወገድ አለበት። የስፖርትን ውጤቶች በድግምቱና በአስማቱ የማስተካከል ችሎታ ያለው ቢኖር አፍሪካ በሁሉም ስፖርት የዓለም ሻምፒዮን በሆነች ነበር።

ይህ ሁሉ የይድነቃቸው ትግል ቀላል አልነበረም። በተለይ በአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን ፕሬዝዳንትነታቸው ወቅት ወደ ስፖርቱ ዘልቀው መግባት ያቃታቸው ኩባንያዎች ለይድነቃቸው ተሰማ ተቃዋሚዎች ድጋፍ ያደርጉ ነበር። ከ1965-1985 ዓ.ም. የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌደሬሽን ዋና ጸሓፊ ሆነው ያገለገሉት አቶ ካሣ ገ/ጊዮርጊስ ይህ ክሥተት በሌጎስ የካፍ ፕሬዝዳንትነት ምርጫ ላይ ታይቷል ብለዋል። በ1980 ዓ.ም. የሌጎስ የካፍ ምርጫ ላይ ይድነቃቸው ለድጋሚ ምርጫ ሲቀርቡ፣ ተቃዋሚአቸው ደግሞ ከዛምቢያ ለመጀመሪያ ምርጫ በዕጩነት ቀረቡ። የዛምቢያው ዕጩ የፕሬዝዳንትነት ምርጫ ይሳካ ዘንድ በርካታ የንግድ ኩባንያዎች ከጎናቸው





ተሰለፉ። በአንጻሩ ይድነቃቸው ለአፍሪካ አገራት ተወካዮች ከጎናቸው አሰልፈው የቀረቡት ግን ለአፍሪካ ሳይታክቱ በታታሪነት የፈጸሟቸውን ተግባራትና ወደ ፊት የሚፈጽሙትን ዕቅድ ብቻ ነበር። ለአፍሪካ እግር ኳስ መታገላቸውንና አብዛኛው ዘመናቸውም በዚያ የትንቅንቅ ጉዞ ማለፉን ደግሞ ኮንፌደሬሽኑን ለሚያውቁ አገሮች ሁሉ ሌላ ምስክር አላስፈለጋቸውም። ስለሆነም ምርጫውን ይድነቃቸው ተሰማ በከፍተኛ የድምፅ ልዩነት አሸነፉ።

ዕድሜያቸውን ሙሉ ከስፖርት ዓለም ያልተለዩት ይድነቃቸው ተሰማ ከአገር ውስጥ እስከ ዓለም አቀፍ የስፖርት አስተዳደሮች ያልሠሩበት ቦታ ጥቂት ነው። ሊሳው ቀርቶ ሰውነታቸው በሕመም በተዳከመበትና በሕይወት ለመቄየት አሥጊ በሆነበት ሰዓት እንኳ ከሠላሳ ዓመታት በላይ በፕሬዚዳንትነትና በምክትል ፕሬዝዳንትነት ያገለገሉትን የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን (CAF) እንቅስቃሴ ከማገዝ አልተቆጠቡም ነበር።

በኢትዮጵያ ሬዲዮ ረጅም ዓመታት በተወዳጅ የስፖርት ጋዜጠኝነት ያሳለፈው አንጋፋው የስፖርት ጋዜጠኛ ደምሴ ዳምጤ ይድነቃቸው ከታላቅ ተጨዋችነት፣ አሠልጣኝነትና መሪነት በተጨማሪ የተዋጣላቸው ተንታኝና የአድማጭን ጆሮ መሳብ የሚችሉ ተናጋሪ እንደ ነበሩ መስክሯል። በዓለም ዋንጫና በአፍሪካ ዋንጫ ውድድር ወቅት የይድነቃቸው ተሰማ ትንታኔ ይናፈቃል። የስፖርታዊ ክሥተቶች ታሪካዊ ቅደም ተከተል የማይዛነፍባቸው፣ የግጻ ባሕርያትን ስምና የሚገኙበትን ክለብ መቼ ምን እንደ ሆነ ሳይቀር ዐውደ ጥበባዊ በሆነ የመረጃ ስፋትና ምርጥ ቃላት ጎሊና ገዢርና አሳማኝ የንግግር ችሎታ ነበራቸው።

ይህ ማንነታቸው በሕዝቡ ዘንድ ጎልቶ ይታወቅ እንደ ነበረ «እሸቱ ከጃንሜዳ» በሚገባ ገልጾታል፦

> ... ባለፈው ጊዜ የዓለም የእግር ኳስ ዋንጫ ውድድር በቴሌቪዥን ሲተላለፍ የቡና ቤቱ ሁሉ መቀመጫ ተጣቦ ነበር። ይህንን ያየ አንድ ወጣት "አሁን ምን ይጋፋናል?



ይድነቃቸው ሲመጡ ሬዲዮ ብናዳምጥ የበለጠ እንረዳ የለምን?' ሲል የተናገረው ጆሮዬ ገብቷል። ስለ እርሳቸው የሚነገር ሁሉ ጆሮ የሚገባውን ያህል በጆሮ ገቡ ድምጻቸው ጥቃቅኗን ነገር ሳይተዉ ሳያንዛዙ ሲያወጉ ወሬ ሳይሆን ፊልም የሚታይ ያስመስሉታል።

ይድነቃቸው ተሰማ ለማንበብ የማይታክቱ ሰው መሆናቸው ሌላው ተሰጥዎአቸው ነበር። «በንጋ በጠባ ቍጥር ዓለምና ስፖርት እንዴት አደሩ ብለው ሳይጠይቁ ወደ ሌላ ተግባር አይሸጋገሩም ነበር»። ከንባብ ቋሚ ልምዳቸው ጋር በተያያዘም እንደ ሁነኛ ውጤት ሊጠቀሱ የሚችሉ ልዩ ልዩ ሰነዶችን ያረቀቁና የጻፉ ሰው ናቸው። ለሕዝብ ታትሞ በመውጣት ደረጃ እንደ ምሳሌ ሊጠቀስ የሚችለውም «ሕዝብና አስተዳደር፣ ሞራል» የተሰኘው መጽሐፋቸው ነው። በ206 ገጽ ያሰፈሩትን የሕዝብ አስተዳደር ሐሳብ ከማብራራታቸው በፊት የ40 ቃላት ፍቺዎችን በቀዳምያን ገጾች ላይ ለአንባብያን ጽፈው ማቅረባቸው በዚያን ዘመን ይድነቃቸው ምን ያህል ጥንቁቅ ጸሓፊ እንደ ነበሩ ያመላክታል። ለግርማዊ ንጉሠ ነገሥት ማቅረቢያ በጻፉት ቀዳሚ ገጽ ላይ እንደ ገለጹትም፦

> ሕዝብና አስተዳደር በተባለው አርዕስት ሥር ለመጻፍ በሶሻል ሳይንስ የበቃ ትምህርት ማግኘት አስፈላጊ መሆኑን አውቃለሁ። ቢሆንም ልዩ ልዩ መጻሕፍት በማንበብ ራሴ ለመረዳት የቻልሁትን ያህል ሌሎችም ቢያውቁ የሚጠቅም መስሎ ስለ ታየኝ ለማዘጋጀት ደፍሬያለሁ።

ለይድነቃቸው ስፖርት ምን ጊዜም ለሕዝቦች የእርስ በእርስ መቻቻልና የሰላም ቦታ መሆኑን ማረጋገጥ፣ በእምነት እና በዘር ላይ የተመሠረቱ ክለቦች እንዳይኖሩ መጣር ቀዳሚ ዓላማቸውና ተግባራቸው ነበር። ለደቡብ አፍሪካ የፀረ አፓርታይድ ትግልም ስፖርቱን በሚገባ ተጠቅመውበታል። እኒህ ታሪካዊ ሰው በአፍሪካ የስፖርት ኮንግረስ፣ በዓለማቀፍ ኦሎምፒክ ኮሚቴ፣ በፊፋና በአፍሪካ ኦሎምፒክ ኮሚቴ በፕሬዚዳንትነትና በሌሎች ከፍተኛ የአመራር





ኀላፊነት ቦታዎች ሁሉ ተመድበው አገልግለዋል።

የአፍሪካ መሪዎች የፈረንጆቹ 2007 «የአፍሪካ እግር ኳስ ዓመት» እንዲሆን በወሰኑበትና የካፍ 50ኛ የምሥረታ ዓመትን አስመልክቶ በኢትዮጵያ በተከበረበት ወቅት፣ የእኒህ ትጉህ ኢትዮጵያዊ ሕያው አገራዊ ሥራ በመሪዎች ተዘክሮ ታላቅ አድናቆት ተችሮታል። «የአፍሪካ እግር ኳስ ዓመት» እንዲከበር ሐሳብ ያቀረቡት ጠቅላይ ምኒስተር መለስ ዜናዊ ሲሆኑ፣ የካፍ ፕሬዝዳንት ኢሳ ሃያቱና የፊፋ ፕሬዚዳንት ጆሴፍ ሴፕብላተር ኢትዮጵያዊውን ይድነቃቸው ተሰማን «ለእግር ኳስ ስፖርት ክብር የተፈጠሩ ሰው» ብለው አወድሰዋቸዋል። ይኸው የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽን አምሣኛ ዓመቱ ላይ ከአህጉሪቱ ጠንካራ ድርጅቶች መካከል አንዱ ሊሆን የበቃው ይድነቃቸው ተሰማን የመሳሰሉ መሪዎቹ በጣሉት መሠረት እንደሆነ ተነግሯል። የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌደሬሽንን (CAF) በአህጉሪቱ የተደነቀ አፍሪካዊ ድርጅት ለማድረግ ያሰቡት ውጥን ሠምሯል። በሊሎች ክፍላተ ዓለም ያዩአቸውን መልካም አሠራሮችና ጠቃሚ ናቸው ብለው የሚያስቧቸውን ሕጎች ተግብረዋል። ኮንፌደሬሽኑን በገንዘብ አቅምና በአደረጃጀት ተስፋ ወደሚሰጥ የእድገት እርከን አሸጋግረውታል። ይድነቃቸው ተሰማ ለአፍሪካ ስፖርት ያደረጉት ተጋድሎና ያሳዩት የሥራ ምግባር ከፍተኛ ጽናትንና የመንፈስ ጠንካራነትን ይጠይቅ ስለ ነበርና እርሳቸውም ይህንን በብቃት ስላሳዩ በሰሜን አፍሪካ ትይዩ በስፔን ግርጌ ባለው ታላቅና ጽኑ አለት ስም «የአፍሪካው ጂብራልታር» በመባል ተሰይመዋል። እንዲሁም እ.አ.አ በ1975 ዓ.ም. በሰሜናዊቱ አፍሪካ ሞሮኮ በካዛብላንካ ከተማ የሚገኘው ስታዲየም በስማቸው ተሰይሟል።

ይህንን ሁሉ አኩሪ ተግባር በትጋት ቢያከናውኑም ለሠላሣ ዓመታት ለስፖርት የሰላም መድረክነትና ለጥቁር ሕዝቦች የስፖርት ዓለም ስኬታማነት የታገሉት ሰው ማንም ባልጠበቀው ሰዓት አለፉ። የወቅቱ የፊፋ



ፕሬዝዳንት ጆ ሀቫላንጅ «በአፍሪካ እግር ኳስ የተዋጣለት መሪ ነበር። ለእግር ኳስ ስፖርት መስፋፋት ከፍተኛ ድርሻን ተወጥቷል። በፊፋ መርሀና እንቅስቃሴ ውስጥም ትልቅ ድርሻ የነበረው ሰው» በማለት የይድነቃቸውን ብርቅዬ ማንነት ገልጸውታል።

ይድነቃቸው ተሰማ ሕይወትን በዕቅድና በዓላማ መርተዋል። እያንዳንዷን ደቂቃ ለታላቅነት በተሠራ ሥራ ውስጥ መዝነዋታል። የስፖርት ነገር ሁሉም ነገራቸው፣ የእግር ኳስ ሜዳ አየር እስትንፋሳቸው ሆነው አልፈዋል። ለአፍሪካና ለኢትዮጵያ ስፖርት ጊዜያቸውን ሁሉ ያጠፉት ሰው በመጨረሻ ዘመናቸው በካንሰር ሕመም እየተሠቃዩ እንኳ የቻሉትን ያህል ሠርተዋል። ለአፍሪካ ዘርፈ ብዙ ሚና የተጫወቱ ሰው በኢትዮጵያውያን ቀመር ነሐሴ 13 ቀን 1979 ዓ.ም. ሕይወታቸው ሲያልፍ አፍሪካን ከባድ የሐዘን ድባብ ተጫናት።

በርካታ የካፍ ባለሥልጣናትም ለአፍሪካ ክብርና ኅብረት በአፍሪካ ሕዝቦችና በሌላው ዓለም መሀል አንድነትና ወዳጅነት እንዲፈጠር የታገሉ ሰው አረፉ ብለዋቸዋል። በወቅቱ የኢንተርናሽናል ኦሎምፒክ ኮሚቴ ፕሬዝዳንት አንቶኒዮ ሳማራንችም «ከኦሎምፒክ እንቅስቃሴ ታሪክ ውስጥ ዋናው የስፖርት መሪና ተደናቂ ሰው» ብለዋቸዋል።

የአፍሪካ ስፖርት እንቅስቃሴ ዋነኛ አደራጁን አጣ። ካሜሩን ትሪቢዩን በወቅቱ፣ «የአፍሪካን የስፖርት መድረክ የድንጋጤና መራር ሐዘን ድባብ ዋጠው» ሲል እ.ኤ.አ በ 1987 ባወጣው ጽሑፍ ላይ አስፍሯል።

ከሕፃናት ቡድን አምበልነት እስከ ከፍተኛ የስፖርት መሪነት በታላቅ ትግል የደረሱት ይድነቃቸው ሲሰናበቱን፣ የአፍሪካ እግር ኳስ ዓለም አቀፋዊ ዝና እንዲያገኝ አድርገው ነው። በተለያዩ ባህሎችና ቋንቋዎች የተከፋፈለችው አፍሪካን እግዚአብሔር በተሰጣቸው ጥበብ በስፖርት የጋራ ቋንቋነት





እንደ አህጉር አድርገው ለረጅም ጊዜ ለመምራት ችለዋል። በእግር ኳስ ተጫዋችነት፣ አሠልጣኝነት፣ በካፍ ፕሬዚዳንትነት፣ በፊፋ አባልነትና በሌሎችም ባለፉባቸው በርካታ ኃላፊነቶች ሁሉ የማይጠፋ መልካም አሻራቸውን ትተው አለፉ።

ለአፍሪካ የስፖርት አባት ምስጋና ይግባና ዛሬ የአፍሪካን እግር ኳስ የሚንቅ ዓለም ዐቀፍ ማኅበረ ሰብ የለም። በአህጉሪቱ እንዲፋፋ የጣሩለት ስፖርት ዛሬ ለአፍሪካ ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ችግሮች አጋዥ መፍትሔ እየሆነ መጥቷል። ጥቍር ከዋክብት ይናቁባቸው በነበሩ የአውሮፓ መድረክ ላይም የእንቁ ያህል ውድ ሆነዋል። ካፍም እግር ኳሱም አድገዋል። ከዚህ ሁሉ በስተ ጀርባ እንግዲህ ለስፖርቱ ዕድሜያቸውን ለመሠዋት የደፈሩት፣ ለሕጎች ተግባራዊነትና ለአህጉሪቱ መብት የታገሉት ኢትዮጵያዊው ሰው ናቸው - ደማቁ ይድነቃቸው ተሰማ።

## መወድስ

**የስፖርቱ ተንታኝ ፍልሱፍ ረቂቅ**
**የአፍሪካ አንበሳ የፋት ቦሉ ሊቅ**
**የኳስ ቦንዳሳ በሜዳ ጕልህ**
**ደማቅ ታሪክህ ይነገርልህ**



## ትምህርተ ውልብታ

የሙያ ስኬት ሙያን ጠንቅቆ ከማወቅ የሚመጣ ነው

የተቋም እድገት ያለ ቆራጥ መሪ አይሆንም

አህጉራዊ ታዋቂነት በመንደር ውስጥ ካለ ትንሽ ነገር ይጀምራል

ማንበብ ሁሉንም ሙያ የሚመግብ የማደጊያ መንገድ ነው






## የውልብታ ምንጭ


Confederation Africaine de Football (CAF) 1957-199. Published to celebrate its 40th year anniversary. (1997)

Tadele Yidnekackew Tessema In the world and in the world of sport. United publishers (1981) Addis Ababa.

Cameroon Tribune. N"3950-SAMEDI 22 AOUT 1987

ይድነቃቸው ተሰማ ፣ሕዝብና አስተዳደር፣ ሞራል፣ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት 1954 ዓ ም አዲስ አበባ

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ታሪክ አዲስ አበባ ኢትዮጵያ 1967

የካቲት መጽሔት 11ኛ ዓመት ቊጥር 5/1980 እሸቱ ከጃንሜዳ፣«በምድር ይድነቃቸው»

ከትምህርት ዓለም፣ ቅጽ 11 ቁ 1 መስከረም 1982 ዓ. ም. «ትምህርትና ስፖርት» ይድነቃቸው ተሰማ (ክፍል ሁለት)

Http: www. Ethio sports. Com /Ydnekachew. html smar, 2007

http:// www. CAF online. org.

ቃለ ምልልሶች የይድነቃቸው ተሰማን ህይወት አስመልክተው በቴሌቪዥን የተላለፉ የታዋቂ ግለሰቦች አስተያየቶች 1993






## የአንባቢው የግል ማስታወሻ







**አለ ፈለገሰላም**
**1915 –**
**አለ ተማጠኑ ለበላይ**
**ሥዕል በኢትዮጵያ እንዲሆን ዘመናይ**

በእውነት የአገሬ ልጆች ስላስታወሱኝና የሠራሁትንም ሥራ ስላልረሱ ተደስቻለሁ። አሁንም ያለኝ ከፍተኛ ምኞት በአገሬ በኢትዮጵያ ጥበብ እንዲፋፋና ጠቢባን እንዲበዙ ነው።

ጣሊያን በወረራ ከገባ ብዙም አልቈየም፤ አንድ ቀን አያቴ እንደ ተኙ ሳያዩኝ ከቤት ወጣሁ። ከባልንጀራዬ ጋር አብረን ነበርን። ራት ብሎ ልጆች ሲጫወቱ በማየታችን ተቀላቀልን። በመሐከል አንድ የጣሊያን አሽከር የነበረ ሰው እኔ እጅ ላይ የነበረችውን ዱላ አይቶ አማረችው መሰለኝ "አምጣ" አለኝ። እኔ ምንም ከመናገሬ በፊት አብሮኝ ያለው ባልንጀራዬ "ለምን አምጣ ትለዋለህ በራስህ ዱላ ተጫወት" ይለዋል። በዚህ ጊዜ አሽከሩ ተናደደና ባልንጀራዬን በያዘው ዱላ ጭንቅላቱን መታው። የመታው ክፉኛ ስለ ነበር መሬት ላይ ወደቀ። በዚያን ጊዜ እኔ ንዴትም ድንጋጤም ይዞኝ በያዝሁት ዱላ የመቺውን አናት ባለኝ ኀይል መታሁት። እሱም ወደቀ። ከባልንጀራዬ ጋር ተያይዘን በሩጫ ወደ ቤት ገባን። በኋላ ለካ ያ የጣሊያን አሽከር 'ጭጭ' ብሏል። በማግሥቱ ቤት ድረስ መጥተው ወደ እስር ቤት ወሰዱኝ። አራት ቀናት ያህል ያለ እህልና ውሃ በእስር ቤት ካቈዩኝ በኋላ "የሞት ፍርድ ተፈርዶብሃል" ብለው ከሌሎች እስረኞች ጋር ይዘውኝ ወደ ገደል አፋፍና ጫካ ወሰዱኝ።

ስንደርስ አካፋ ሰጡንና የምንቀበርበትን ጕድጓድ እንድንቈፍር አዘዙን። ድንጋጤም ልጅነትም አለ፤ ብቻ ለመቈፈር እየሞከርሁ አካባቢዬን ቃኘሁ። ከምንቈፍርበት አጠገብ ትልቅ ገደል አለ። ከኋላዬ መሣሪያ የያዙ የጣሊያን ወታደሮች ቆመዋል። አንዳንዶቹ ያወራሉ። አንዱ ከነኔ ራት ብሎ ሲጋራ ያጨሳል። መሞቴ ካልቀረ ለምን አልሮጥም ስል አሰብሁ ። አካፋውን ወርውሬ በገደሉ ቍልቍል እግሬ እንደ መራኝ ሮጥሁ። መሣሪያ የያዙት ሁሉ የተኰሱ ይመስለኛል። ከኋላዬ የተኩስ ድምፅ ይሰማኝ ነበረ። በኋላ ገደል ውስጥ ገባሁና በቅጠል ተሸፍኜ ድምፄን አጥፍቼ ተቀመጥሁ። ወታደሮቹ ቢያደምጡ ድምፅ የለም፤ ቢያዩ የሚንቀሳቀስ ነገር የለም። ስለዚህ ከጥይት ቢያመልጥ እንኳ ገደል ስለ ገባ ይሞታል ብለው ትተውኝ ሄዱ። ቤተ ሰቦቼ ታዲያ ሞቷል ብለው ለቅሶ ላይ ነበሩ። መትረፌን ያወቁት ዘግይተው ነው።



ይህንን ታሪካቸውን ያጫወቱን በአገር ውስጥና በውጭ አገር ብዙ ለሞት የሚያደርስ አደጋ የተፈታተናቸው ሆኖም ሁሉን አልፈው



የዕድሜ ባለ ጠጋ የሆኑት የሥዕል ጥበብ ባለ ራእዩ አለ ፈለገ ሰላም ናቸው።

የአዲስ አበባ ሥነ ጥበብ ትምህርት ቤትን አመሠራረት በማንሣት የ85 ዓመቱን አዛውንት የሕይወት ታሪክ በመጠኑ ለመዳሰስ ይቻላል። ምክንያቱም እሳቸው በሥነ ጥበብ ትምህርት ቤቱ ታሪክ ውስጥ ፣ ትምህርት ቤቱ ደግሞ በእርሳቸው ታሪክ ውስጥ እንደ ተዋደዱ አሉና። የመጀመሪያው የዘመናዊ ሥዕል ጥበብ መምህርና የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤቱ መሥራች በመሆናቸው እርሳቸውና ትምህርት ቤቱ ተሳስረዋል።

በርካታ ሠዐልያንን ስላፈራውንና በማፍራትም ላይ ስለሚገኘው ትምህርት ቤት አመሠራረት ሲናገሩ ለሰማቻቸው፣ ብቻቸውን ታግለው ምሥረታው እንደ ተሳካላቸው ማስተዋል ይቻላል። ከትምህርት ቤቱ ተመርቀው ግሩም የሆነ የሥዕል ጥበብ ባለቤት በሆኑ ወጣትና ጕልማሳ ሠዓልያን ቡሩሽ ውስጥ፣ የእኚህ አዛውንት ታሪክና ጥረት እንደ ቀለመ ዘልቋል። በዚህም የብዙ ሠዓሊያን አባት ተብለዋል። ዛሬ አዛውንቱ ዕድሜያቸው ገፍቶአል። ሆኖም ከዓመታት በፊት ያለውን ታሪክ ሲያወጉ ቀልብን ይገዛሉ።

አቶ አለ ፈለገሰላም ሰሜን ሸዋ ፍቼ ከተማ በ1915 ዓ.ም ተወለዱ። የሁለት ወር ጨቅላ ሳሉ አባታቸውን በድንገተኛ ሞት ተነጠቁ። የአባታቸው አባት፣ ማለትም የአለ አያት፣ በሞት ያጡትን ልጃቸውን እያስታወሱና፣ መልከ መልካሙን ሕፃን እየተመለከቱ ልጁ አልሞተም፤ አምሳያውን ተክቷል ሲሉ ሕፃኑን «አለ» ብለው ሰየሙት። በሁለት ወር የሕፃንነት ዕድሜአቸው አባታቸውን ያጡት አቶ አለ፣ ሁለት ዓመት ሲሆናቸው ደግሞ እናታቸው ለሌላ ባል በመዳራቸው ምክንያት ተለዩአቸው። በዚህም ምክንያት ዕድገታቸው በአባታቸው አባት በአለቃ ጎሩይና በአባታቸው እናት በወ/ሮ አፀደ ደስታ ኀላፊነት ሥር ሆነ።



አያታቸው አለቃ ኅሩይ እንዲሁም የአለ አጎት የሆነው የኅሩይ ልጅ እምአእላፍ፣ በጊዜያቸው የታወቁ ሠዓልያን ነበሩ። አለቃ ኅሩይ መንፈሳዊ ሥዕሎች በመሥራት ሲታወቁ፣ እምአእላፍ ኅሩይ ደግሞ መንፈሳዊና ዓለማዊ ሥዕል በመሣል ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት ተቀጥረው ይሠሩ ከነበሩቱት ቀደምት ሠዓልያን መካከል አንዱ ነበሩ። አቶ አለ ዕድሜያቸው ከፍ እያለ ሲመጣ የአያታቸው ዕድሜ በመግፋቱ ሥዕል ከእርሳቸው ለመማር እንዳልቻሉ ይናገራሉ፦

> አያቴ ስለ ሣሏቸው የቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሥዕሎችና ከዚህም የተነሣ የታወቁ ሠዓሊ እንደ ነበሩ ሲወራ እሰማለሁ። በተረፈ ለእኔ ያሳዩኝ ነገር የለም። እንዲያውም እኔን የላኩኝ የቅኔ ትምህርት እንድማር ወደ ዲቁና ነበር። ጥቂት ጊዜ መንፈሳዊ ትምህርት ተማርሁ። ብዙ ሳይቈይ በጣሊያን ጦርነት ጊዜ በአርበኝነት ዘምቶ የነበረው አጎቴ እምአእለፍ ኅሩይ ከጦርነቱ መልስ የቤተ ሰብን ደኅንነት ለመጠየቅ መጣ። ወደ አዲስ አበባ ሲመለስ እኔን «አንተ መማር ያለብህ ዘመናዊ ትምህርት ነው።» በማለት ይዞኝ ተመለሰ። በወቅቱ በጦርነት ችግር ተዘግተው የነበሩት ትምህርት ቤቶች ሁሉ የተከፈቱበት ጊዜ ስለ ነበረ፣ አጎቴ ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት አስገባኝ። ከዚህም የተነሣ ከጦርነቱ በኋላ በተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ከገቡት የመጀመሪያዎቹ ተማሪዎች መካከል አንዱ ሆንሁኝ።

ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት ተማሪዎችን ተቀብሎ ማስተማር ከጀመረ ከአንድ ዓመት በኋላ ተማሪዎች የደንብ ልብስ /ዩኒፎርም/ እንዲለብሱ ተወሰነ። ለደንብ ልብሱም «ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት» የሚል ያጌጠ ባጅ ለመሥራት ውድድር ቀረበ። የባጅ ውድድሩንም አለ አሸነፉ። የሚገርመው ግን የአቶ አለ አያት አለቃ ኅሩይ ለአጼ ምኒልክ አንድ ሰው ለመንግሥታቸው



የተቀኘውን ቅኔ በሥዕል ኀድፍ በማስቀመጣቸው ለመንበራቸው ዐርማ እንዲሆን ተደርጓል። አጎታቸው እምአእላፍ ደግሞ የአድዋ ጦርነትን በሥዕል ገልጾ በታሪክ ተመዝግቦለታል። አሁን



ደግሞ ከዚያው ከአለቃ ኅሩይ ቤት የተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ባጅ ውድድር በአቶ አለ አሸናፊነት ተመዘገበ። በዚን ጊዜ ነው ሥዕል የመሣል ችሎታውም ደሙም እንዳላቸው ርግጠኛ የሆኑት። በመቀጠልም በተፈሪ መኮንን ትምህርት ቤት ውስጥ የሚያስተምር አንድ ጣሊያናዊ መምህር የአንዲትን ሴት ምስል ሲሥል ተመለከቱ። እሳቸውም ባዩት መሠረት ጓደኞቻቸውን ለመሳል ሞከሩ። በትምህርት ቤቱ ውስጥ በአለ የተሣሉትን የጓደኞቻቸውን ምስል ያየ ሁሉ አደነቀላቸው። ከወራት በኋላ አቶ አለ ችሎታቸውን በማዳበር በትምህርት ቤቱ ውስጥ የሠሩዋቸውን የተለያዩ ሥዕሎች ለተማሪዎችና ለመምህራን ለእይታ አቀረቡ። ገንዘብ ያላቸው ሁሉ ሥዕሎቻቸውን በመግዛት አበረታቷቸው። ይህ የአለ የታሪክ ምእራፍ በእንዲህ ዓይነት መልኩ እየተጓዘ ሳለ ፣ ሌላ የሥዕል ታሪክ ምእራፍ ይከፈታል፤ ይህም ተፈሪ መኰንን ትምህርት ቤትን ተተግኖ የመጣ የአለ የውጭ አገር የትምህርት ዕድል ነው።

ወደ ውጭ አገር ሔደው ዘመናዊ የሥዕል ትምህርት እንዲማሩ የረዳቸውን ገጠመኝ ሠዓሊው በማስታወስ እንዲህ ይገልጹታል፦

> አንድ ቀን ግርማዊነታቸው ተማሪዎችን ለመጐብኘት ወደ እኛ ትምህርት ቤት መጡ። በጕብኝታቸው መሀል የእኔን ሥዕሎች ተመለከቱና «ይህን የሣለው ማነው?» ሲሉ ጠየቁ። እኔ እንኳ በአጋጣሚ ከልጆቹ መሀከል አልነበርሁም፤ ግን መምህራኑ ስሜን ጠርተው እኔ መሆኔን ነገሯቸው። በማግሥቱ ንጉሡ ይፈልጉሃል ተብዬ ቤተ መንግሥት ሔድሁ። ንጉሡም ከዚያን በፊት በሌላ ትምህርት አንደኛ በመውጣቴ ሸልመውኝ ነበር። ከሌሎች ልጆችም ጋር ወደ ውጭ አገር ለትምህርት ትሄዳላችሁ ተብለን በማናውቀው ምክንያት ሳንሄድ ቀርተናል። አሁን ከፊታቸው ቆሜ ሲያዩኝ አስታወሱኝና፦ «አንተ እስከ አሁን አልሄድህም እንዴ?» ሲሉ ጠየቁኝ። እኔም ንጉሥ ሆይ አለሁ አልኳቸው። «በል አሁን ጥሩ ሠዓሊ ሆነህ ተገኝተሃልና ወደ ውጭ አገር ሔደህ ሥዕል ተማር» በማለት ሰላዘዙ ሁኔታዎች ሁሉ



በአፋጣኝ ተከናውነው አሜሪካ አገር ቺካጎ አርት ዩንቨርስቲ ራሴን አገኘሁት።

ሠዓሊ አለ ቺካጎ ዩንቨርስቲ ለአምስት ዓመታት ከተማሩ በኋላ በ 1946 ዓ.ም በጥሩ ውጤት በBA ዲግሪ ተመረቁ። ከዚያም አንድ ዓመት በመጨመር የማስተማር ዘዴን ተማሩ። ወደ አገራቸው ከመመለሳቸው በፊት ከሥዕል ጋር የተያያዙ ሥራዎችን በመሥራት ጥቂት ገንዘብ ከአጠራቀሙ በኋላ በጣሊያንና በፈረንሳይ አገሮች በመዘዋወር አገሮቹ የደረሱባቸውን የሥዕል የዕድገት ደረጃ ጎበኙ። ከዚያም ለአገራቸው የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤትን የመመሥረትን ሐሳብ «ፀንሰውና» ለመሥራት ያቀዱትን ትልቅ ተግባር ይዘው በ1947 ዓ.ም. ወደ አገራቸው ኢትዮጵያ ተመለሱ።

በወቅቱ ኢትዮጵያ ከብዙዎች የአፍሪካ አገሮች በጥበብ ቀዳሚ የነበረች አገር ስትሆን፣ የምትታወቀውም፣ በመንፈሳዊ ሥዕሎቿና እንዲሁም የአክሱምና የላሊበላን ሐውልቶች በመሳሰሉት የሥዕልና የቅርጻ ቅርጽ ጥበባት ነው። እኒህ የሥዕል መምህር ያካበቱትን ዕውቀት ይዘው መመለሳቸው ደግሞ አገራችን በሥዕል ጥበብ ረዥም ርምጃ የተራመደችበትንና ዘመናዊ አካሄድን የተከተለችበትን ምቹ ሁኔታ ፈጠረ።

ከቺካጎ እንደ ተመለሱ ሌሎች ተማሪዎችም እንደሚያደርጉት፣ ንጉሡ ፊት ቀርበው እጅ ሊነሡ ገቡ። «እንኳን ደኅና መጣህ» ከተባሉም በኋላ በተማሩት ትምህርት ምን መሥራት እንደሚፈልጉ ተጠየቁ። እርሳቸውም «በአገራችን የሥዕል ትምህርት ቤት እንዲከፈትና የኔም ተግባር በሚከፈተው የሥዕል ትምህርት ቤት ማስተማር እንዲሆን እፈልጋለሁ» በማለት ለንጉሡ አገራዊ ሽክማቸውን ገለጹ። ለጊዜው ይህንን በሚመለከት ምንም የተሰጣቸው ምላሽ ባይኖርም፣ ትምህርት ሚኒስቴር ተመድበው በልጆች መማሪያ መጻሕፍት ላይ ሥዕሎችን





መሥራት ጀመሩ። ይሁን እንጂ በውስጣቸው የነበረውንና እያደገ የመጣውን የሥዕል ትምህርት ቤትን የመክፈት ራእይ ከንጉሡ ዘንድ በተለያየ የሥራ ምክንያት በገቡ ቍጥር ማንሣታቸው አልቀረም። ሆኖም በትምህርት ቤቱ ጉዳይ ንጉሡ «ጊዜው ሲደርስ ይሆናል» ከሚለው የማስታመሚያ ሐሳብ በቀር ሌላ ተግባራዊ ምላሽ ስላልሰጡ፣ ሠዓሊ አለ ፈለገ የራሳቸውን ጥረት ለመቀጠል ቍርጥ ውሳኔ አደረጉ።

> በመጀመሪያ እኔ ራሴ የምኖርበትን ቤት ራስ ደስታ አካባቢ ተከራየሁ። በግቢው ውስጥ ጣሊያኖች የሠሯቸውና ለማስተማሪያም ምቹ የሆኑ ሁለት ትልልቅ መጋዘኖች ነበሩ። ከዚያ በራሴ ወጪ ለመማሪያ የሚሆኑ ዕቃዎችን ገዛሁና ቍጥራቸው ከአሥራ አምስት የማይበልጡ የሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎችን ቅዳሜና እሑድ መጋዘኑ ውስጥ ማስተማር ጀመርሁ። ነገሩ ለእኔም የመንፈስ ደስታ ሰጠኝ፤ ልጆቹም ተደስተው ጥሩ ጥሩ ሥዕሎችን መሥራት ጀመሩ። ጥቂት ተማሪዎች ያገኙት ዕድል በነሱ ብቻ ተወስኖ መቅረት የለበትም ብዬ በአካባቢው ባሉ ትምህርት ቤቶች በመዞር «ሥዕል ለመማር የምትፈልጉና ፍቅሩ ያላችሁ ሁሉ ከዚህ ቦታ ኑ፤በነጻ ልትማሩ ትችላላችሁ» በማለት ጥሪ አደረግሁ። የተማሪው ቍጥር ከገመትኩት በላይ ጨመረ። ክቡር ከበደ ሚካኤል (ዶክተር) የዚያን ጊዜ ትምህርት ሚኒስቴር ነበሩ። እየመጡ የተማሪዎችን ሁኔታ ይጐበኙ ነበር። እኔም ከትምህርት ሚኒስቴር ፈቃድ ጠየቅሁና በሰፊው ማስተማር ቀጠልሁ። ክረምት ሲመጣ በጣም ብዙ ተማሪዎች መጡ።

መምህሩ ሠዓሊ አለ ረጅም ርቀት የማያስኬድ በሚመስለው ርምጃቸው ውስጥ ብሩህ ተስፋ ታያቸው። ከዓመታት በፊት ወደ ቺካጎ ዩንቨርስቲ ሄደው ይህን ዕውቀት እንዲያገኙ ያደረጋቸውን አጋጣሚ አስታወሱ። ከተማሪዎቻቸው ጋር በመሆን ሥራዎቻቸውን ለእይታ ለማቅረብ መዘጋጀት ጀመሩ። ተማሪዎች አስቀድመው ከሠሩት ሥዕሎች ውስጥ ጥሩ ጥሩውን በመምረጥና በተጨማሪም አዳዲስ ሥዕሎችን በመሥራት የእርሳስ ንድፍ



ሥዕሎችን፣ የውሃና የዘይት ቀለም ሥዕሎችንና ቅርጻ ቅርጻችን አዘጋጁ። በመምህሩ የመጀመሪያ ተማሪዎች የተዘጋጀው ትእይንት ሥዕል ፣ ዛሬ በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ ሥር ተጠቃሎ «በአዲስ አበባ ዩንቨርስቲ የሥነ ጥበብ ዲዛይን ትምህርት ቤት» በመባል ለሚታወቀው ትምህርት ቤት ጅማሬ መሠረት ጣለ። ወደ ትእይንት ሥዕሉ ለተጠሩት የኤምባሲ ተወካዮች፣ ንጉሣዊ ቤተ ሰቦችና ታዋቂ ሰዎች መምህሩ የመክፈቻ ንግግር አደረጉ፤ በንግግራቸው ውስጥም፣ «በአገራችን የሥዕል ትምህርት ቤት እንዲመሠረት የመላው ሕዝብና የእኔም ምኞት ነው። ለዚህ ደግሞ የእያንዳዳችሁ ድጋፍ ያስፈልጋል። እነዚህን ሥዕሎች ስትገዙ ለዚህ የሥዕል ትምህርት ቤት ድጋፍ መሆኑን እያሰባችሁ ይሁን» የሚል ይገኝበታል። በዕለቱ ወደ 78 ሺህ የሚጠጋ ብር ተሰበሰበ። መምህሩም በራሳቸው ጥረት ያገኙትን ገንዘብ ይዘው ወደ ንጉሡ በመሄድ፣ <<እኔ ይህንን ያህል ገንዘብ አሰባስቤአለሁ፤ መንግሥት ደግሞ የራሱን ድጋፍ አድርጎልን ትምህርት ቤቱ በአፋጣኝ እንዲጀመር ይሁንልን>> ሲሉ ጠየቁ። ጥያቄያቸው ተቀባይነት አግኝቶ በአስቸኳይ 150 ሺ ብር እንዲጨመርላቸው ታዘዘ።

የአለን ፈር ቀዳጅነትና የንጉሡን ይሁንታ ያገኘው የትምህርት ቤቱ ግንባታ፣ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተጠናቀቀ። አራት ትልልቅ የማስተማሪያ ክፍሎች፣አንድ ሰፊ ምድር ቤትና ፎቅ ያለው የሥዕል ማሳያ አዳራሽ /Gallery/፣ ስድስት የመምህራን ቢሮዎች፣ አንድ የዳሬክተር ቢሮና አንድ የጸሐፊ ቢሮ የያዘ ሕንጻ ኀምሳ ተማሪዎችን ለማስተማር የሚበቃ ሆኖ ተዘጋጀ። ይህ ትምህርት ቤት ሐምሌ 16 ቀን 1950 ዓ.ም፣ በንጉሡ የልደት ቀን፣ በራሳቸው በንጉሠ ነገሥቱ ተመርቆ ተከፈተ። በዕለቱ በንጉሠ ነገሥቱ የተነበበው መሪ ቃል፦



እኛም ይህ የሥነ ጥበብ ትምህርት መስጫ ሕንጻ እንዲሠራ የፈቀድነው በዚህ ጥበብ ታላቅ ሞያ ያላቸው ወጣቶች ሁሉ ጥንታዊውን አሠራር ሳይለቁ፣ ከዘመናዊ አሠራር ጋር እያዋሐዱ፣ የኪነ ጥበብ ሥራ በአገራችን እንዲታደስና ይበልጥ



እየተስፋፋ እንዲሄድ የማድረጉን ጉዳይ ታላቅ ቁም ነገር ስለምንሰጠው ነው። በዚህም ኢትዮጵያ የሥልጣኔን ባህልና መንፈስ ተከታይ መሆኗን ለማሳወቅ የሚደረገው ጥረት ድጋፍ ይሆናል ብለን ተስፋ የምናደርግበት ነው። የፈጣሪያችንን ሥራ የምናደንቀው ለሥጋችን ጠቃሚ እንዲሆን በሠራው ነገር ብቻ ሳይሆን በሥነ ፍጥረት ውስጥ የሚገኙትን ነገሮች ሁሉ በመመልከትና በመመራመርም ጭምር መሆን ስለሚገባው፣ በዚህ በኩል የሚኖረንን ፍላጎት በሥነ ጥበብ ሥራ አማካይነት ልናገኝ እንችላለን።

በማለት ንጉሣዊ መሪ ቃላቸውን አስተላለፉ። አለ ፈለገ ሰላምን «አለ ተማጠነ ለበላይ፣ ሥዕል በኢትዮጵያ እንዲሆን ዘመናይ» የሚያሰኛቸውም ይኸው ስኬታማ ውትወታቸው ነው። የሥነ ጥበብ ትምህርት ቤቱም ማስተማር ሲጀምር አቶ አለ ዲሬክተር ሆነው ከመሥራታቸው በተጨማሪ፣ ተማሪዎችን የቀለም ቅብና የንድፍ ሥራ ትምህርቶችን ያስተምሩ ነበር።

የሥዕል ትምህርት ቤቱ ሥራ ከጀመረበት ጊዜ አንሥቶ ከአቶ አለ ፈለገሰላም ጋር በሥራ ባልደረባነት የሠሩት አቶ ብሥራት በቀለ ሲናገሩ፦ «እኔ ከትምህርት ሚኒስቴር ተመድቤ ወደ ሥዕል ትምህርት ቤት በመዛወር አስተዳደር ሆኜ በ1951 ዓ.ም ተቀጠርሁ። አቶ አለን የማውቀው ከዚያ ጊዜ አንሥቶ ነው። በሥራ ላይ እጅግ ታታሪና ዕውቀቱን ማካፈል የሚወድ፣ ከልቡ የሚያስተምር ሰው ነው። ትምህርት ቤቱ ሥራ በጀመረ ጊዜ ብዙ ውጣ ውረድን አሳልፏል። በወቅቱ ትምህርት ሚኒስቴር ትኩረት የሚሰጠው ለቀለም ትምህርትና የቀለም ትምህርትን ለሚያስተምሩ ትምህርት ቤቶች እንጂ ሙያ ለሚያስተምሩት አልነበረም። በተለይም ለትምህርት ቤቱ ለሚያስፈልጉ ነገሮች በጀት ከትምህርት ሚኒስቴር ለማስፈቀድ አቶ አለ ብዙ ይቸገር ነበር። ይሁን እንጂ ችግሩን ሁሉ በዘዴ ያልፈው ነበር።» በማለት የአቶ አለ ፈለገ ሰላምን አስተዋይነትና ብልኀ መሪነታቸውን ይገልጻሉ።



የሥነ ጥበብ ትምህርትን በመደበኛ ትምህርትነት መቀበል ለትምህርት ሚኒስቴር ባለ ሥልጣኖች እንግዳ የሆነ ነገር ነበር። ከዚህ የተነሣም ለልዩ ልዩ የጥበቡ ዘርፎች አስፈላጊ የሆኑትን መርጃ መሣሪያዎች በበጀት አስፍሮ ለማጸደቅ ከፍተኛ ትግል የሚጠይቅ ጉዳይ ነበር። በተለይ የማስተማሪያ ሞዴል በበጀት ውስጥ በሚካተትበት ጊዜ፣ ለዚህ የሚወጣው ወጪ አስፈላጊ እንደ ሆነ ስለማይታሰብ «ምንድነው ሞዴል የሚባል ነገር ቢቀርስ?» እየተባለ በአቶ አለ ፈለገ አመራርና በትምህርት ቤቱ አገልግሎት ላይ ችግር ይፈጠር ነበር። በእንዲህ ዐይነቱ ፈታኝ ጊዜም አቶ አለ የሚኒስቴሩን ጽሕፈት ቤት ባለ ሥልጣኖች ሞዴል ማለት ምን ማለት እንደ ሆነ ያውቁ ዘንድ ትምህርት ቤት ድረስ ይዘዋቸው ለመምጣት ይገደዱ ነበር። አቶ ብሥራት ይህንን ሁኔታ ሲያብራሩ ፦ «ሰዎቹ ሞዴሉ ርቃኑን ወደ ቆመበት ክፍል ሲገቡ ሁሉም ደንግጠው ወጡ። ከዚያ በኋላ ገንዘብ ለሞዴል ሲባል ያ ርቃኑን ያዩት ሰው ትዝ እያላቸው ሳይሆን አይቀርም ያለ ምንም ችግር ይሰጥ እንደ ነበረ አስታውሳለሁ። ሌላ ጊዜ ደግሞ እንዲሁ ተማሪዎች ንድፍ ሲያጠኑ ከሚጠቀሙባቸው የተለያዩ ቍሳቍሶች ጋር በተገናኘ አንድ አጋጣሚ ተፈጠረ ፤ የሰውንና የእንስሳትን የራስ ቅል በመጠቀም መሣል በሥዕል ትምህርት ውስጥ የተለመደ ስለሆነ፣ አንድ ጊዜ ተማሪዎች ለጥናት የሰው የራስ ቅል ይዘው ተገኙ ተብሎ ወደ እስር ቤት ተወሰዱ። አቶ አለ ይህን ሲሰሙ ተነሥተው ፖሊስ ጣቢያ ሄዱ። ነገሩን በቀላሉ ሊረዱለት ስላልቻሉ ጉዳዩ በዚያን ጊዜ የፖሊስ አዛዥ ወደ ነበሩት ጄኔራል ፅጌ ዲቡ ደረሰ። እና ጉዳዩን አብራርተው ስላስረዳ ልጆቹ እንዲለቀቁ ሆነ» በማለት ይገልጻሉ። አቶ አለ ከተማሪና ከአስተማሪዎች ጋር እንዲሁም ከብዙ ባለ ሥልጣናትና ከታላላቅ ሰዎችም ጋር ጥሩ ግንኙነት ስለ ነበራቸው፣ ተማሪዎች ወደ ውጭ አገር ሄደው ለመማር የትምህርት ዕድል እንዲያገኙ ያደርጉና በትምህርታቸውም ችግር እንዳይገጥማቸው ይከታተሉ ነበር።



አቶ አለ በትምህርት ቤቱ ውስጥ የደርግ መንግሥት ሥልጣን እስከ ያዘበት 1966 ዓ.ም. ድረስ ሲሠሩ ከቈዩ በኋላ ትምህርት ቤቱ በባህል



ሚኒስቴር ሥር ሲሆን እርሳቸው ወደ ቅርስ ጥገና ተላኩ። የቅርስ ጥገና ኀላፊ በመሆን ለአምስት ዓመታት ሠሩ። በዚህም ሥራቸው ላይ እያሉ በደርግ ጊዜ በየመሥሪያ ቤቱ እንደሚደረገው ሁሉ የርእዮተ ዓለም ውይይት አድርግ የሚል ትእዛዝ ስለ ተሰጣቸው፣ <<እኔ መንፈሳዊ ሰው ስለ ሆንሁ ይህን ትእዛዝ አልቀበልም>> በማለት ሥራውን ለቀቁ።

አቶ አለ በአገራችን የሥዕል ታሪክ ውስጥ የመጀመሪያው የሥዕል ትምህርት ቤት ዲሬክተርና መምህር ከመሆናቸው በተጨማሪም በአገራችን መንፈሳዊ ሥዕል ታሪክ ውስጥ በአርአያነት የሚጠቀሱ ሠዓሊ ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ አራት ኪሎ አካባቢ የሚገኘውን የሥላሴ ቤተ ክርስቲያን ፣ የመርካቶ ሚካኤልን፣ የመርካቶ ራጉኤልን፣ የመካኒሳ ብሥራተ ገብርኤልንና የአምስት ኪሎ ቅድስት ማርያምን ቤተ ክርስቲያኖች የውስጥ ሥዕሎች በከፊልና በሙሉ ሥለዋል። ከአዲስ አበባ ከተማ ውጭ ደግሞ የቍልቢ ገብርኤልን፣ የናዝሬት ማርያምን፣ አሜሪካ ዋሽንግተን የመድኀኔ ዓለምን አብያተ ክርስቲያናት ሥዕሎች ሥለዋል። አያታቸው አለቃ ኅሩይና አጎታቸው አምአእላፍ ኅሩይም በመንፈሳዊ ሥዕሎች ሥራ ተጠቃሾች ነበሩ። እኒህ ባለ ታሪክ ናዝሬት ያለችውን የማርያም ቤተ ክርስቲያን ሥዕል ለመሥራት ወደዚያ ሄደው አገሩን በመውደዳቸው ለሃያ ስድስት ዓመታት ያህል በናዝሬት ኖረዋል። በያዝነው ዓመት ወደ አዲስ አበባ ተመልሰው ጦር ኀይሎች አካባቢ በመኖር ላይ ይገኛሉ።

አቶ አለ ይህ ፍጻሜው ያማረ ጥረታቸው በቅርቡ ወደ አሜሪካ አገር የሚሄዱበትን አጋጣሚ ፈጥሮላቸዋል። ጕዟቸውን ወደዚያ ያቀኑት በሁለት ሺው ዓመት ማክተሚያ ሰኔ ወር ውስጥ ነበር። አሜሪካ በሚኖሩ ኢትዮጵያውያን የተመሠረተ «ሲድ» የተባለ ድርጅት ታላቅ ሽልማት አበርክቶላቸዋል። ሲድ ይህን ሽልማት እንዲቀበሉ የወሰነው፦ «በሥዕልዎ ባሕላችንን ስለ ገለጹና ዘመናዊ የሥዕል ጥበብን ለኢትዮጵያ ስላስተዋወቁ» ነው ብሏል። ይህ



የአለ የሽልማት አቀባበል ሥነ ሥርዐት የተካሄደው በዋሽንግተን ከተማ በርካታ ኢትዮጵያውያንና የውጭ አገር ዜጎች ባሉበት ነው። አቶ አለ፦ «በእውነት የአገሬ ልጆች ስላስታወሱኝና የሠራሁትንም ሥራ ስላልረሱ ተደስቻለሁ። አሁንም ያለኝ ከፍተኛ ምኞት በአገሬ በኢትዮጵያ ጥበብ እንዲፋፋና ጠቢባን እንዲበዙ ነው» በማለት ደስታቸውንና የወደ ፊት ምኞታቸውን ገልጸዋል።

አቶ አለ፣ መሠረት አለ እና ቴዎድሮስ አለ የሚባሉ የሁለት ልጆች አባት ሲሆኑ ይህ የሕይወታቸው ውልብታ ሲዘጋጅ፦ «የ 85 ዓመት አዛውንት ብሆንም እስካሁን ሙሉ ጤነኛ ነኝ፣ መኪና እየነዳሁ ወደምፈልገው ቦታ ደርሼ እመለሳለሁ። ቤት ውስጥ ያሻኝን ሥራ እሠራለሁ። በዚህም እግዚአብሔርን አመሰግናለሁ።» ብለዋል። እውነትም ጠንካራና ቀልጣፋ ናቸው። የአካል እንቅስቃሴ ያደርጋሉ፤ ዓሣ ያጠምዳሉ፣ ሥዕልም ይሠራሉ። በሥዕል ጥበብም የተማሪዎቻቸውን ተማሪዎች፣ የልጅ ልጅ ልጅ ዓይተዋል። ቅድመ አያትም ሆነዋል።





<u>መወድስ</u>

ለኢትዮጵያ ሥዕል አምላክ ሲያስብለት
አለ አመለጠ ከፋሽቶች ጥይት

ቀለሙን ነከረ ሸራውን ወጠረ
ጥበቡን ሊጠበብ የዘሩን ቄጠረ

የፈረንጁን ሥዕል ተምሮ መጣና
ዐውዶ ገብ አረገው በኢትዮጵያ ቃና

የንጉሥ ደጅ ጠንቶ ወትውቶ ለበላይ
ሥዕልን በኢትዮጵያ አረገው ዘመናይ

<u>ትምህርተ ውልብታ</u>

ርእይ እውን ሆኖ ለማየት የሚያስከፍለው ዋጋ መጨረሻ ላይ የራሱን ክብር ይዞ ይመጣል።

በየደረጃው የምንወስዳቸው ቁርጥ አቋሞችና ጽናት የሕይወትና የሙያ ድሎቻችን ዓይነተኛ ምስጢሮች ናቸው።





## የውልብታ ምንጭ

ታዬ ታደሰ የኢትዮጵያ ጥናትና ምርምር ተቋም ሙዚየም፣
አንዳንድ የታወቁ የኢትዮጵያ ሠዓሊዎች አጭር
የሕይወት ታሪክ 1962 እስከ 1950 ዓ.ም.
ዩናይትድ ፕሬስ አዲስ አበባ 1977 ዓ.ም.

ጦማር መስከረም 28 ቀን 1995 ዓ.ም.

ኔሽን (ኪነ ጥበብ) ታኅሣሥ 24 ቀን 1996 ዓ.ም.

ሩሕ ሐምሌ 12 ቀን 1994 ዓ.ም.

ከአቶ አለ ፈለገ ሰላም ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ ሚያዚያ
1999





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ











፱



## እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ
## 1916–
## የሙዚቃ አርቅቆ ምናኔን ተጣብቆ

አበቦች ውብ ልዕልቶች፣ ዛፎች ደግሞ እንደ ጠባቂዎቻቸው፣ ነፋስ ወጣት መልእክተኛ፣ ፀሓይ ደግሞ የዓለም ሁሉ ንግሥት ሆነው ይታዩኝ ነበር

ገና ከጧቱ ጣቶቻቸው የሙዚቃ ቅኝትን መንደራቸው ያደረጉ በመሆናቸው ፒያኖና ኦርጋን ዳሳሽ፣ ቫዮሊን ተዝጋሻርም ናቸው። ትንፋሻቸውም የዳበረው በዋሽንት ሽቅብና ቊልቊል እያለ ነው። የዕብራይስጥ ቋንቋ የአፍ መፍቻን ቋንቋን ያህል አቀላጥፈው ይናገራሉ። ከሌሎች ቋንቋዎች በተጨማሪ ፈረንሳይኛና ጀርመንኛ ቋንቋዎችን ያለ አንዳች መደናቀፍ፣ አንብበው ተናግረውና ጽፈው ይጠቀሙባቸዋል። ገና ከማለዳው መንኵሰው ያለ ዕድሜአቸው አንቱ በሚያሰኝ የሕይወት መንገድ ውስጥ በመግባታቸው እማሆይ ወይም እናት ሆይ ናቸው። ገዳማዊ ዝንባሌአቸው ታሪካቸውን ለብቻ እንድናይ ቢያደርገንም፣ ተሠጥዎአቸውና ክዋኔአቸው ግን ከአንጋፋዎቹ የአውሮፓ የረቂቅ ሙዚቃ አቀናባሪዎች ተርታ ያሰልፋቸዋል። ለምን ቢባል አብዛኞዎቹ የአፍሪካ አገሮች በቅኝ አገዛዝ የፖለቲካ ሥርዐት ሥር በወደቁበት የ19ኛው ክፍለ ዘመን ኢጋማሽ በረቂቅ ሙዚቃ አቀናባሪነትና ተጫዋችነት ከነጻዪቱ ኢትዮጵያ የፈረንጆቹን ፒያኖ አርቅቀው በመጫወት ብቅ ማለት የቻሉ ብርቅ ሴት በመሆናቸው ነው። ከመቶ በላይ የሚሆኑ ረቂቅ የሙዚቃ ድርሰቶችን በፒያኖ ያቀናበሩት ታላቅ ሴት እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ ናቸው።

እማሆይ በዚያን ዘመን በነበረው ማኅበረ ሰብ ውስጥ እንግዳ በሆነ አመለካከት ታይተው ነበር። የሙዚቃ ባለ ሙያነት በጊዜው ተቀባይነት ያልነበረው ከመሆኑም በላይ፣ ሴት ሆነው ኢትዮጵያውያን ፈጽሞ የማያውቁትን የሙዚቃ ቅንብራቸውን ይዘው መድረክ ላይ ብቅ ማለታቸው ደግሞ ዘመኑን የተገዳደረ ነበር።

ከምንኵስናቸው በፊት የውብዳር ገብሩ ይባሉ የነበሩት እማሆይ ጽጌ ማርያም ገብሩ በታኅሣሥ ወር 1916 ዓ.ም. በአዲስ አበባ ከተማ ተወለዱ። መማር የብርሃን ኑሮ መሆኑ ከገባቸውና በብርሃኑም ከሚመላለሱ ከከንቲባ ገብሩ ደስታ መወለዳቸው ጥሩ የጠዋት ዕጣ ሆኖላቸዋል። ከዚህም የተነሳ በወቅቱ በኢትዮጵያ መደበኛ ትምህርት መስጠት ባለመጀመሩ ምክንያት ዕድሜአቸው ስድስት





ዓመት ሲሆን ከታላቅ እኅታቸው ከስንዱ ገብሩ ጋር ለትምህርት ወደ ስዊዘርላንድ ተላኩ።

ስዊዘርላንድ ሞንቲማራል በሚገኘው የሴት ተማሪዎች ዐዳሪ ትምህርት ቤት ውስጥ ገብተው ትምህርታቸውን ለመከታተል በቁ። በዚያም በቅድሚያ ቫዮሊንና ፒያኖ አጠኑ። ይህን እንጂ እያደር ለፒያኖ ያላቸው ፍቅር አመዝኖ ቫዮሊንን ማሠለስ ጀመሩ። በስዊዘርላንድ እያሉ የሙዚቃ ትምህርታቸውን በሚማሩበት ወቅት በሰባት እና በስምንት ዓመት ዕድሜያቸው ገደማ ከሥነ ፍጥረት ጋር መቀራረብና መወዳጀት ያዙ።

> አበቦች ውብ ልዕልቶች፣ ዛፎች ደግሞ እንደ ጠባቂዎቻቸው፣ ነፋስ ወጣት መልእክተኛ፣ ፀሐይ ደግሞ የዓለም ሁሉ ንግሥት ሆነው ይታዩኝ ነበር። ዐዳሪ ተማሪ ቤት ውስጥ ብቸኝነት ከሕፃንነት ጀምሬ ጓደኛ ሆኖኝ ዐብሮኝ አደገ። ... ሙዚቃ እወድ ነበርና ስሰማ የሐዘን ስሜት ይፈጥርብኝ ነበር። ለገና ስጦታ ለገና አባት ደብዳቤ ጽፌ ቫዮሊን ጠይቄ ሲሰጠኝ ወዲያው አስተማሪ ታገልኝ መማር ጀመርኩ። በሌላ በኩል የአስተዳዳሪው ዘመድ የሆነች አንዲት ልጅ ፒያኖ ስትጫወት እየተመለከትኩ እኔም እየተፍጨረጨርሁ መምታት ቻልኩ። ከዚያም የመጀመሪያ ሙዚቃዬን ቀመርሁ። ስሙን ሲጠይቁኝ (The Storm) ነው አልኳቸው [ትርጓሜውም] ዶፍ ማለት ነው።

ከዚያም የውብዳር (እማሆይ ጽጌ) ከአምስት ዐመት የስዊዘርላንድ ቈይታ በኋላ አሥራ አንድ ዓመት ሲሆናቸው ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው ትምህርታቸውን ቀጠሉ።[1] ይህ በእንዲህ እንዳለ በግንቦት 1928 ዓ.ም. አዲስ አበባ በጣሊያኖች እጅ ስትወድቅ በ1929 ዓ.ም. መጀመሪያ የውብዳር (እማሆይ ጽጌ) እና ከፊል ቤተ ሰቦቻቸው በኢጣሊያ ከምትገኘው ከሳርዲኒያ በስተ ሰሜን ወደ አዚናራ ደሴት፣ ቈይቶም በኔፕልስ አቅራቢያ ወደ ምትገኘው ሜርኮግሊያኖ ተዛወሩ።

---

[1] በዚያን ጊዜ የእቴጌ መነን ትምህርት ቤት ተከፍቶ ሥራ ጀምሮ ነበር።



በአገር ውስጥ ደግሞ በወረራው ዘመን አባታቸው ከንቲባ ገብሩ ቤተ ሰቦቻቸውን ይዘው በመጀመሪያ ወደ ነቀምት፣ ከዚያም ወደ ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ ወደ ጎሬ ሄዱ። በወረራው ሳቢያ እማሆይ ሁለት ወንድሞቻቸውን ከማጣታቸው በላይ የሙዚቃ ጥናታቸውም ተስተጓጉለባቸው።

ከወረራው በኋላ የውብዳር (እማሆይ ጽጌ) በራሳቸው ጥረት የጽሕፈት መኪና ተምረው ስለ ነበር በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት በጸሓፊነት ሲሠሩ ቈዩ። ነገር ግን በጊዜው የነበራቸው ሐሳብ ወደ ፈረንጅ አገር ሔዶ በዚያው መማር ስለ ነበር፣ እንደገና አባታቸው ጃንሆይን ፈቃድ እንዲጠይቁላቸው በማድረግ ወደ ካይሮ ሄደው የሙዚቃ ትምህርታቸውን ቀጥለዋል።

ግብጽ ደርሰውም አሌክሳንደር ኮንቶርዊችዝ በተባሉ ሊትዋኒያ ቪልኒየስ ኮንዘርቫቶሪ ትምህርት ቤት በተማሩ ፖላንዳዊ መምህር አማካኝነት የቫዮሊን ትምህርት መማር ጀመሩ። መምህራቸው ኮንቶርዊችዝ በካይሮ ዩኒቨርስቲ በሮያል ኢንስቲቲዩት የሙዚቃ ክፍል ኀላፊ የነበሩ ሲሆን፣ በንጉሥ ፋአድ ቤተ መንግሥትም እየተገኙ የሙዚቃ ኮንሰርት ያቀርቡ የነበሩ ታላቅ የሙዚቃ ሰው ናቸው።

ከሁለት ዓመት የግብጽ ቆይታቸው በኋላ፣ ማለትም በ1938 ዓ.ም. በካይሮ በተከሰተው ከፍተኛ ሙቀት የተነሣ የውብዳር ወደ ኢትዮጵያ ተመለሱ። በተመሳሳይ ጊዜም መምህራቸው ኮንቶሮዊችዝ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።[2]

የውብዳር ገብሩ ከግብጽ ሲመለሱ የ21 ዓመት ዕድሜ ወጣት ነበሩ። ኢትዮጵያ ውስጥ ጥቂት እንደ ተቀመጡ ከንጉሣዊ ቤተ ሰብ የሆነ አንድ ሰው ወደ እንግሊዝ አገር ሄደው ለሁለት ዓመት መማር የሚያስችላቸውን የቅድሚያ ክፍያ አጠናቀቀላቸው።



[2]እኚህ ሰው እንደ መጡም ንጉሥ ኃይለ ሥላሴ «በቤተ መንግሥት ውስጥ የሙዚቃ ኮንሰርት ምሽቶች አዘጋጅ» በሚል ኃላፊነት የክብር ዘበኛ የሙዚቃ ባንድ ዲሬክተር አድርገው ሾሟቸው። ከዚያን ጊዜ አንሥቶ ወደ ሰሜን አሜሪካ እስከ ሄዱበት እስከ 1940 ዓ.ም ድረስ ኮንቶርዊችዝ በኢትዮጵያ የሙዚቃ መስክ ከፍተኛ አገልግሎት አበርክተዋል።



ዳሩ ምን ያደርጋል ትምህርታቸውን ለመከታተል ከፍተኛ ጕጕት ቢያድርባቸውም የውብዳር ወደ ውጭ ሄደው መማር የሚያስችላቸው የይለፍ ፍቃድ እንዳይሰጣቸው ከበላይ በስጠው ትእዛዝ የተነሣ ተከለከሉ። በዚህም የከፍተኛ ትምህርት ምኞታቸው በመቀጨቱ የሞት ያህል ከባድ ወደ ሆነ የልብ ሐዘንና ተስፋ መቍረጥ ውስጥ ገቡ።

ኮሎኔል ዳዊት ገብሩ በመጽሐፋቸው ስለዚህ ጉዳይ እንዲህ ብለዋል

> ይህ ልክ እኔ የደረሰብኝ ዐይነት ነው። አባቴ በ1922 ዓ ም ወደ አሜሪካ አገር ሲሄድ ኢየሩሳሌም አድርሶኝ ለትምህርት ወደ ጀርመን ሊልከኝ ቢያስብም፣ የትምህርት ሚኒስትሩ ባህሌ ጸዳሉ ተመሳሳይ ዕግድ በማድረግ የትምህርት ዕድሌን አጨናገፉብኝ። ግን እኔ ብዙ ስላየሁ ቻልኩት። እኅቴ ግን አልቻለችውም።

የውብዳርም በበኩላቸው በማስታወሻቸው ላይ የሚከተለውን አስፍረዋል ፦

> የመጨረሻ ዕድሌ በመሰበሩ መንፈሴ ተሰባብሮ ሞትን ብቻ ፈለግሁ። ከአሥራ አምስት ቀን በላይ እህልና ውሃ ሳልቀምስ ባዶ ጥቍር ቡና ብቻ እየጠጣሁ ስስነብት ያው የሞት ጥላ በላዬ ላይ ሲያንዣብብ፣ የመጨረሻ ቍርባን እንዲሰጡኝ ጠይቄ አንድ ቄስ እስከ ነበርሁበት ምስካይዬ ሕዙናን መድኀኔ ዓለም አጠገብ እስከ ነበረው ሆስፒታል ድረስ መጥተው አቈረቡኝ። የዚህ ሀለም ፍቅርና የመኖር ፍላጎት ከኅሊናዬ ፈጽሞ ተወገደ።

የውብዳር ከሕመማቸው አገግመው ሙሉ ጤነኛ ሲሆኑ በክብር ዘበኛ መምሪያ ውስጥ ሥራ ጀመሩ፤ ከዚያም የንግድ ሥራ ትምህርት ጀመሩ። ይሁን እንጂ መንፈሳቸው በፍጹም ሊረጋጋ አልቻለም። ከዚያም ጊዜ በኋላ ከዚህ ዓለም ሥርዐት ተለይተው ወደ መንፈሳዊ ዓለም ለመግባት ወሰኑ። የሚታያቸው ነገር መላው ሕይወታቸውን ወደ መንፈሳዊ ሥራ



መልሰው ለእግዚአብሔር አገልግሎት እየሰጡ መኖር ብቻ ሆኑ ። በዚህ መንገድ የሚወስዳቸውን አቋራጭ አቅጣጫ እያብሰለሰሉ ሁለት ዓመት ሙሉ ሌሊት ሌሊት ቤተ ክርስቲያን ሰዓታት ያድሩ ነበር። በዚህ ሁኔታ ሰዓታቱም፣ ቅዳሴውም፣ ሥራውም ላንድ ቀን እንኳ ሳይቋረጥባቸው ቈዩ። በመጨረሻ የሁለት ወር ፈቃድና የሁለት ወር ደመወዝ ተቀብለው ከአንድ ዓመት በፊት ከእናታቸው ከወ/ሮ ካሣዬ ኤለምቱ ጋር ሄደውበት ወደ ነበረውና በወሎ ክፍለ አገር ወደሚገኘው ግሸን ማርያም በመስከረም ወር 1940 ዓ.ም ለሽርሽር ነው የምሄደው በማለት ከቤተ ሰባቸው በድብቅ ኰበለሉ።

በዚያም ለሁለት ዓመት ያህል የቀሳውስቱን ልብስ በማጠብና እንጀራ በመጋገር ለገዳሙ አገልግሎት አበረከቱ። ስለ ሁኔታው በማስታወሻቸው ላይ እንዲህ ሲሉ ጽፈዋል፦

> አቡነ ሚካኤል የተባሉ የገዳሙ አስተዳዳሪ በጥሩ ተቀብለውኝ ሲያነጋግሩኝ፣ ለመመንኰስ መፈለጌን ስነግራቸው፣ 'ዘመዶችሽ በኋላ መጥተው ቢያስቸግሩሽስ?' ብለው ሲጠይቁኝ እኔም ኰስተር ብዬ በነፍሴ የሚያዝባት ሰው ከእኔ ሌላ የለም አልኳቸውና ወዲያውኑ አባ ደሳለኝ የሚባሉትን የደሴ ግቢ መርቆርዮስ አስተዳዳሪ እንዲላጩኝ ጠየቋቸው። አባ ደሳለኝ ሲላጩኝ እጃቸው ብዙ ጊዜ ሲንቀጠቀጥ ምን ሆነው ነው ብዬ ዘወር ብዬ ሳያቸው፣ እንባ አውጥተው ሲያለቅሱ አየሁና 'ምነው አባቴ ምን ሆኑ?' ብላቸው 'አባቴ እንኳ ሲሞቱ አላለቀስሁም፣ እንዲያው አዝኜ ነው' አሉኝ። እኔም 'ምን ለጠጕር ነው የሚያዝኑ' ብዬ ቀላለድሁባቸው፤ 'እንኳንስ ጠጕርን ሌላም በነበረኝ ለጌታዬ አልኳቸው' ።

የውብ ዳር ከዚህ ጊዜ በኋላ መስከረም 21 ቀን 1940 ዓ.ም አስኬማ ለብሰው፣ ቆብ ደፍተው፣ እማሆይ ጽጌ ተብለው የምንኵስና ስም ተቀበሉ። ነገር ግን በመነኰሱ በጥቂት ጊዜያት ውስጥ እኅታቸው ወ/ሮ ገነት ወሬ ሰምተው ገዳሙ ድረስ መጡ። ቤተ ሰቡ ሁሉ በምንኵስናቸው የተነካ እንደ







ተረበሹና ለሕመም እንደ ተዳረጉ እኅታቸው ነግረዋቸው በሌሎችም መነሻሳት ግፊት ከእኅታቸው ጋር ገዳሙን ለቀው ወደ አዲስ አበባ ተመለሱ።

እማሆይ ጽጌ አዲስ አበባ ከመጡ በኋላ ስለ ግሸን ማርያም ደብረ ከርቤ ቦታ ለእቴጌ መነን ነግረው ቦታው ገዳም እንዲሆን ጥረት አድርገው ነበር። ለጊዜው ሐሳባቸው የንጉሡን ይሁንታ ቢያገኝም እንኳ፣ ነገሩ በእንጥልጥል ቀረ። የውብዳር በመነኰሱ በሁለተኛው ዓመት አባታቸው ከንቲባ ገብሩ ዐረፉ። በዚህም ጥልቅ ሐዘን ተሰማቸውና ተመልሰው ወደ ግሸን ሄዱ። ከዚያም እንዲሁ እየሄዱ እየመጡ አሥር ዐመት ካስቈጠሩ በኋላ ወደ ጎንደር አመሩ።

እማሆይ ጽጌ ማርያም በ1950ዎቹ መጀመሪያ ላይ ጎንደር ገዳም ውስጥ በነበሩበት ዘመን የመጀመሪያውን ታዋቂና ተወዳጅ የሆነውንና በፒያኖ የተጫወቱትን ረቂቅ ሙዚቃ በሸክላ አስቀረጹ። ይህን የሙዚቃ ሸክላ ለማስቀረጽ የገፋፋቸው ምክንያት ወደ ጎንደር በሄዱበት ጊዜ ከግሸን የሚወዱትን የጎንደርን የቅኔ ማሕሌት አገልግሎት ቤተ ክርስቲያን አድረው ሰምተው ሲመለሱ፣ ባላገር ወጣቶች በየሜዳው ተኝተው ተመለከቱ። ወጣቶቹን ሲጠይቋቸውም መጠጊያ የሌላቸው በመሆናቸው ጐዳና ላይ እንደሚያድሩ ይነግሯቸዋል። በዚህም ልባቸው እጅግ በጣም ተነካ። ካለቻቸው የፒያኖ ችሎታ በቀር ምንም ጥሪት አልነበራቸውምና ሸክላ አስቀርጸው ለእነዚያ ችግረኞች መጠለያ ለመሥራት ተመኙ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ እማሆይ ጽጌ አዲስ አበባ መጥተው በፓትሪያርኩ ጽሕፈት ቤት ጸሐፊት፣ እንዲሁም በቅዱስ ሲኖዶስና በውጭ ግንኙነት ረዳት ጸሐፊት በመሆን የሠሩ ሲሆን፣ ሰላማዊ ኑሮ ቢያገኙም እናታቸው በመካከሉ እየሩሳሌም መሄድ ስለ ፈለጉ በ1948 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ በንጉሡ ንጉሥ መልካም ፈቃድና ችሮታ ከእናታቸው ከወ/ሮ ካሣዬ ኤለምቱ ጋር በመሆን ወደ ኢየሩሳሌም ሄዱ። እናታቸውም በዚያው ዓመት የኢየሩሳሌም ሊቀ ጳጳስ በነበሩት በብፁዕ



አቡነ ፊልጶስ ምንኵስናን ተቀብለው ከሁለት ወር ቈይታ በኋላ ወደ ኢትዮጵያ መጡ።

እማሆይ ጽጌ በመነኵሴ በ19 ዓመታቸው እንደገና ከእናታቸው ጋር ለሁለተኛ ጊዜ በ1959 ዓ.ም ወደ ኢየሩሳሌም ሄደው እስከ 1964 ዓ.ም በቈዩበት ጊዜ፣ በኀላፊነትና በመዝገብ ቤት ሠራተኛነት እንዲሁም የገዳሙን የቤት ኪራይ በመሰብሰብ አገልግለዋል። በ1959 ዓ.ም በእስራኤልና በዐረብ አገሮች መካከል በተደረገው የስድስቱ ቀን ጦርነት እስራኤል ባለ ድል ሆና ኢየሩሳሌምን የግዛቷ ክፍል ስታደርግ፣ የገዳሙን ጳጳስ ጠይቀው ደብረ ገነት የተባለውን ቦታ የሴቶች ገዳም እንዲሆን አደረጉ። እማሆይ ጽጌ ማርያምም የገዳሙ እመ ምኔት ተብለውም ተሾሙ።

በኢየሩሳሌም ገዳም ውስጥ አምስት ዓመት ከኖሩ በኋላ በተማሩና ባልተማሩ መነኮሳት መካከል አለመግባባት ተፈጠረ። በዚያም ምክንያት እማሆይ ሰላማቸው ስለ ደፈረሰ ወደ ኢትዮጵያ ተመልሰው በውጭ ጉዳይ ሚኒስትርና በክብር ዘበኛ ጠቅላይ መምሪያ ተመድበው ሠርተዋል።

አስቀድሞ እንደተገለጸው እማሆይ ጽጌ ማርያም አያሌ የሙዚቃ ቅንብሮች የነበሯቸው ሲሆን፣ ከእነርሱም ውስጥ ጥቂቶቹን ለማስቀረጽ በቅተዋል።

በ1955 ዓ.ም በጀርመንኛ የተቀዱ ሁለት ቅንብሮች (spielt Eigene Komposition) ለእናታቸው ለእማሆይ ካሣዬ መታሰቢያ mutterliebe (mothers love) Ballade der Geister (Ballad of the spirites) Daslied des meers (the song of the sea) Heimweh (home sickness)

Berichet uber mahlet das gebt von St. Yared (essay of mahlet, the prayer of St. Yared.)Der gewittersturm (the storm)



በ 1954 ለወላጅ አልባ ልጆች ማሳደጊያ



የዋለውና በእኅታቸው በደስታ ገብሩ የገንዘብ ድጋፍ አማካኝነት የተቀረጸው ሦስተኛው አልበማቸው።

በ 1964 ዓ.ም በዲዮቆናት አጃቢነትና በኦርጋን በመሰጫወት በእስራኤል የመንፈሳዊ ሙዚቃ (Liturgical music) the hymn of Jerusalem/The Jordan river song/ የዮርዳኖስ ወንዝ ዜማ በሚል ርእስ በእስራኤል እያሉ ያቀናበሩት አራተኛ አልበማቸው። በዚያኑ ተመሳሳይ ዓመት

በ1964 ወደ ኢትዮጵያ በመመለስ ሁለት ኮንሰርቶችን ለሕዝብ አዘጋጁ። ሁለቱም ለበጎ አድራጎት የታሰቡ የሙዚቃ ዝግጅት ኮንሰርቶች ሲሆኑ ገቢው በጊዜው በወሎ ረኃብ ለተጠቁ ወገኖች የሚውል ነበር። Church of Kidane Meheret/yet my king is from old (psalm 74:12) (የኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ቤ/ክ ምስባክ የሙዚቃ ቅንብር)

የቀድሞ ቅንብሮቻቸውን በመጨመር የመጨረሻ አልበማቸውን ኢትዮፒክስ በሚል ርእስ አስቀርጸዋል።

በ1971 ዓ.ም በብሔራዊ ትያትር የኮንሰርት ትዕይንት በየካቲት 1 ምሽት 1:30 ላይ በተፈጥሮና ሰው ሠራሽ በሆነ አደጋ ምክንያት በጊዜው ለተጐዱ ሰዎች መርጃና ማቋቋሚያ እንዲሆን በሚል አቅርበዋል። አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት፣1971

የሰው ልጆች ችሎታ በተለያዩ መልኮችና ይዘቶች ይገለጻል። የእማሆይ ሥራዎች የረቀቀ የሙዚቃ ችሎታ የታየበት ከመሆኑም ባሻገር ሙያቸው ብዙ የሚያነጋግሩ ገጽታዎች እንዳሉት አድናቂዎቻቸው ይናገራሉ። እማሆይ ጽጌ ማርያም ኢትዮፒክስ በተሰኘው ባለ ተከታታይ ውብና ድንቅ አሐዳዊ (solo) የፒያኖ የሙዚቃ ቅንብር አልበማቸው፣ የአንድን አድማጭ ስሜት በመኰርኰር የዓለማችን ምርጥ



የሙዚቃ አቀናባሪዎች ከሆኑት ከዴበሲ እስከ ዋለር እና ቢል ኢቫንስ ድረስ በመሄድ ትውስታ እንዲኖረው ያደርጋሉ።

እማሆይ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የጥሞና ሀሳቦች (meditation) እና ተፈጥሮታዊ ውበት ብዙ ጊዜ የሚያተኩሩባቸውና የሚወዷቸው የቅንብሮቻቸው አርዕስተ ጉዳይ እንደ ነበሩና ቅንብሮቻቸውም በኢትዮጵያ የዜማ ቅኝቶች ዙሪያ የተመሠረቱ ናቸው። የተጽዕኖ ጉዳይ ከተነሣ ምናልባትም በጊዜው የሰሟቸው የእነ ካውንት ቤዚ፣ የኦስካር ፒተርሰን፣ የኬዝ ጃሬት፣ የአብዱላህ ኢብራሂምና በተለይም ኤሪክ ሳቲ የተባሉት የዘመኑ ሙዚቃ አቀናባሪዎች መጠነኛ ተጽዕኖ በእማሆይ ቅንብሮች ላይ ማጥላቱ ይታመናል።

የሙዚቃ አስተማሪና ቀማሪ እንደ ሆነው እንደ አቶ ዕዝራ አባተ እምነት የእማሆይ ጽጌ ማርያም የሙዚቃ ቅንብር ያልተቀላቀለ የረቂቅ ሙዚቃ ስልት የሆነና ቅንብሮቹም የኢትዮጵያን የሙዚቃ ቅኝት የጠበቁ የፔንታቶኒክ ቅኝቶች ናቸው።

ለየት ካለው ከዚህ የሙዚቃ ችሎታቸው የተነሣ 21ኛው grand Ethiopiques series አልበም አሐዳዊ ፒያኖ አቀናባሪ (Solo pianist composer) ለነበሩት ለእማሆይ ጽጌ ማርያም ሥራ በማስታወሻነት ተበርክቷል። እማሆይ ይህ የሕይወታቸው ውልብታ እስከተሰራበት ጊዜ በኢየሩሳሌም ገዳም በምንኩስና ሕይወትና አገልግሎት እንደሚገኙ ይታወቃል።





## መወድስ

**የተፈጥሮን ጸጋ ውበትን አድናቂ**
**ጽጌ ማሪያም ገብሩ እብቢ ድመቂ**
**ተሰናን ነው ታሪክሽ**
**ብርቅ ነው ሙዚቃሽ**

## ትምህርተ ውልብታ

**በወቅቱ ተቀባይነት ያልነበረውን ሙያ ይዘው መውጣታቸው በዚህ ዘመን ያለን እኛም በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ባናገኝ እንኳ ለተረዳነውና ላመንንበት እውነት ጸንተን መቆምንና በዚያም መገስገስን የእማሆይ ውልብታ ያስተምረናል።**

**የሰው የጧት ሕይወት ስጡ (Exposure) የኋላ ዕድሜውን ፈለግ የማስመር ኀይል እንዳለው የሚያሳይ ታሪክ ነው። ይህ ደግሞ ለልጆች ትምህርትና ውሎ በጽኑ እንድናስብ ያደርገናል።**



## የውልብታ ምንጭ

ኮሎኔል ዳዊት ክንቲባ ገብሩ የኢትዮጵያ ቅርስ ቦሌ ማተሚያ ቤት አዲ አበባ፣1985 ዓ. ም.

የሴቶች ክዋኔና ርእይ 1993 የኢትዮጵያ ሴቶች እንቅስቃሴ በ20ኛ ክፍለ ዘመን ጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ንኡስ ጉዳይ ዘርፍ

Mestawet Aragaw, *The Hidden Talented Female Ethiopian Pianist*, senior thesis, Aug. 2006,

አዲስ ዘመን ጋዜጣ የካቲት 1971 ዓ. ም.





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ









# ፲



ተስፋዬ ግህሉ

1916–

የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች

እንደምን አላችሁ ልጆች!

**እንግሊዛዊው ባሳየሁት ነገር ተገረመና፣ ‹አንተ እዚህ ምን ትሠራለህ?› አለኝ ‹አገሬን ስለምወድ ውጪ ወጥቼ መቅረት አልፈልግም›አልኩት።**

ሕፃኑ ሰኔ 12 ቀን 1916 ዓ.ም ባሌ ክፍለ አገር ከጹ በሚባል ሥፍራ ከአቶ ግዛው ኤጀርሳና ከወ/ሮ የወንዝ ወርቅ በለጠ ተወለደ። አምስት ዓመት ሲሞላው ትምህርት ይማር ዘንድ አባቱ ወደ ጎባ ይዘውት ሄዱ። ቤተ ሰቦቹ በሥራ ምክንያት አንድ ቦታ የሚቀመጡ አልነበሩምና ጉዟቸውን ጊኒር ወደሚባል ቦታ አቀኑ። እዚህም ብዙ አልቈዩም። መጀመሪያ ወደ ጎሮ፣ በመቀጠልም ወደ አርከሌ፣ ከዚያ ተመልሰው ደግሞ ሐረር ገቡ። ከቤተ ሰቡ ጋር ከአንዱ ከተማ ወደ ሌላ ከተማ ሲንከራተት የነበረው ህፃን ትንሽ ፋታ ያገኘው ሐረር ከገባ በኋላ ነበር። ትምህርት ቤት ገብቶ «አልፋ ቤት» ፊደል እንዲቈጥር ተደረገ። ትምህርቱን የሚማረው በፈረንሳይኛ ቋንቋ ነበር።

ወላጅ አባቱ አሥራ አራት ዓመት ሲሞላው አቶ መንበረ ወርቅ ኃይሉ ለተባሉ ግለ ሰብ በዐደራ ሰጡት። በዚህ ጊዜ አዳጊው ወጣት የወላጆቹን ቤትና ፊደል የቈጠረበትን ቀዬ ለቅቆ ወደ አዲስ አበባ መጣ። አዲስ አበባ መጥቶ ቀበና አካባቢ ከሚገኘው ኮከበ ጽባህ ት/ቤት ገብቶ ትምህርቱን እንደ ቀጠለ ብዙም ሳይቈይ የማይጨው ጦርነት ተቀሰቀሰ።

የአዳጊው ተስፋ የጨለመው ይሄኔ ነበር። ቤተ ሰቦቹ የሚኖሩት ሐረርና ባሌ በመሆኑ አጎቶቹና አጠቃላይ ዘመዶቹ ሳይቀሩ ወደ ጦርነት ዘመቱ። ከዘመዶች መካከልም ከጦርነቱ የተረፈ አንድም ሰው አልነበረም። ሁሉንም የማይጨው እሳት በላቸው። ወጣቱ በየዕለቱ የሚመጣበትን መርዶ እየሰማ እህህ ማለት ሥራው ሆነ። "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ ከአባቱ በዐደራ የተቀበሉት ብቸኛ አሳዳጊው አቶ መንበረ ወርቅ ኃይሉን አዲስ አበባ ላይ ፋሺስት ጣሊያን ሰቀላቸው።"

ምንም እንኳ ይህ ወጣት በዚህ ቍጭት ከጠላት ጋር ለመፋለም ልቡ ቢንሟሟም በበረታ የእግር ሕመም ሳቢያ ሐሳቡን እውን ማድረግ አልቻለም። እንዲያውም የእግር ሕመሙ ስለ ጠናበት ለሕክምና ወደ ሆስፒታል መሄድ ግድ ሆነበት።





ሆስፒታል ውስጥ እያለም፣ ጥቂት ሲያገግም ኑሮን ለማሸነፍ፣ የሐኪም ቤቱ ኀላፊ የሆነውን ጣሊያናዊ ጫማ ይጠርግ ነበር። ሕክምናውን እየጨረሰ ሲመጣ ከጣሊያናዊው ጋር በመግባባት እግረ መንገዱን መርፌ መቀቀል፣ ቢሮ ማጽዳት የመሳሰሉ ሥራዎች ይሠራ ጀመር። በኋላም ክትባት እስከ መከተብ ደርሶ ነበር። ከዚህ በተጨማሪም ፈረንሳይኛ ቋንቋ በመቻሉ የጣሊያንኛን ቋንቋን ለመልመድ ብዙም ጊዜ ስላልወሰደበት ለሕክምና ለሚመጡ ሰዎች በአስተርጓሚነት ያገለግልም ነበር።

ወጣቱ በዚህ ሆስፒታል ብዙ አልቈየም። አንድ ጣሊያናዊ አትክልት ተራ አካባቢ ክሊኒክ ሲከፍት ይዞት ሄደ። በሆስፒታል ቆይታው የተማረውን የሕክምና ሙያ ከቀጣሪው ጋር በመሆን መሥራቱን ተያያዘው። ጣሊያናዊው ወደ አገሩ ሲሄድ ክሊኒኩ ውስጥ ይታከም የነበረ ሌላ ጣሊያናዊ ከአትክልት ተራ አለፍ ብሎ "ሎምባርዲያ" የሚባል ሆቴል ውስጥ በአስተናጋጅነት ቀጠረው። እግረ መንገዱንም በመስተንግዶ ሙያ አሠለጠነው። ይህ ጣሊያናዊም ብዙ አልቈየም፤ ስለ ታመመ ወደ አገሩ ተመለሰ። ይሁን እንጂ ወደ አገሩ ከመሄዱ በፊት ይህን ወጣት ያኔ እቴጌ ሆቴል እየተባለ በሚጠራው ሆቴል ውስጥ አስቀጠረው። ይህ ታሪክ ከተፈጸመ 60 ዓመት ሆኖታል። በእንዲህ ዓይነት የህይወት ውጣ ውረድ ያለፈው ሰው ግን የአባት ሁሉ መጠሪያ የሆነን ስም ደርቦ በሚሊዮኑ ኢትዮጵያውያንና ኢትዮጵያውያት ዘንድ «አባባ» እየተባለ ዛሬም አለ።

"የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች እንደምን አላችሁ ልጆች!" በማለት ለአርባ ሁለት ዓመታት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ተረት በመተረት ሁለት ትውልድ (አባትንና ልጅን) በመምከር ያሳደጉት አባባ ተስፋዬ የዚህ ታሪክ ባለቤት ናቸው። ታሪካቸውን ከእቴጌ ሆቴል በመቀጠል እንዲህ ሲናገሩም፣ "ሆቴሉን ይመራ የነበረው ጣሊያናዊ ሥልጡን በመሆኑና የወሰደኝ ጣሊያናዊ ዐደራ ስላለበት በጣም ይወደኝ ነበር፡፡ በዚህ ምክንያት የሆቴሉ የምግብ ክፍል ረዳት ኀላፊ አደረገኝ፡፡" ይላሉ።



አባባ ተስፋዬ ለመጀመሪያ ጊዜ ከዘመናዊ ሙዚቃ ጋር የተዋወቁት እዚህ ሆቴል ውስጥ እንደ ነበር ሲገልጹ፣ "ሙዚቃ ስለምወድ ከራርና ማሲንቆ እጫወት ነበር። ሆቴሉ ውስጥ ያገኘሁትን ፒያኖ እየነካካሁ ጥሩ ፒያኖ ተጫዋችም ሆንኩ" ብለዋል። "አንድ ጊዜ ከጣሊያን አገር አርቲስቶች መጥተው ያረፉት እቴጌ ሆቴል ነበር። ትርኢቱን ያቀርቡ የነበረው ሲኒማ ኢትዮጵያ አዳራሽ ስለ ነበር፣ ቀን ቀን የሚበሉትንና የሚጠጡትን ይገዩላቸው ስሄድ የሚሠሩትን በደንብ እመለከት ነበር። ትንሽ ቈይቼ እነሱ ሲሉ የነበሩትን መልሼ እልላቸው ስለ ነበር ይገረሙና፣ <ይሄ ጠቋራ እንዴት ነው የእኛን ቃል የሚጫወተው የኛን ቃል እንዴት ነው የሚናገረው> ይሉ ነበር።"

ይሁን እንጂ የሆቴሉ ሥራና ኑሮ ያን ያህል የተመቻቸ አልነበረም። እንዲያውም ከእርሳቸው በሥልጣን ከፍ ካለው ጣሊያናዊ ጋር እንደማይግባቡ ያስታውሳሉ፤ "ከእኔ በላይ ያለው ጣሊያናዊ ኀላፊ ጥቁር በመሆኔ አይወደኝም ነበር። አንድ ቀን አምሽቼ ወደ ሥራ ገባሁ። ሰሐንና ጭልፋ ይዤ ወደ ምግብ ማብሰያው ስሄድ ያ የማይወደኝ ጣሊያናዊ፣ «እስካሁን የት ቆይተህ ነው አሁን የምትመጣው?» ብሎ በቃሪያ ጥፊ መታኝ። ሰሃኑን አስቀመጥሁና በጭልፋው ግንባሩን አልሁት። የሆቴሉ ኀላፊ ጩኸት ሰምቶ መጥቶ ሲያይ ሰውየው ደምቷል።" የአባባ ተስፋዬና የጣሊያናዊው አለቃቸው ግብግብ በዚህ አልተጠናቀቀም። እየተባባሰ ከመምጣቱ የተነሣ ከአዲስ አበባ ለቅቀው ወደ ሐረር እንዲሄዱ ምክንያት ሆነ። ሌላ መከራ፣ ሌላ ጭንቀት።

"የሆቴሉ ኀላፊ <ማነው እንዲህ ያደረገው ብሎ ሲጠይቅ እኔ መሆኔ ተነገረው። እንጠልጥሎ በርሜል ውስጥ ከተተኝና እንዳልወጣ አስጠንቅቆኝ ሄደ። ፖሊስ ሁኔታውን ሰምቶ ሊይዘኝ ሲመጣ አላገኘኝም። ከሌሊቱ ስድስት ሰዓት ሲሆን ጣሊያናዊው መጥቶ አወጣኝና የሚስቱን ካፖርት አልብሶ ወደ ቤቱ ወሰደኝ። <ነገ በጠዋት ባቡር ጣቢያ እንገናኝ> ብሎኝ ሄደ። በማግሥቱ ባቡር ጣቢያ ስደርስ ጣሊያኑ በካልቾ ብሎ የምግብ ቤት ኀላፊ ለነበረ ሌላ ጣሊያናዊ አስረከበኝ።"





አባባ ተስፋዬ ከአለቃቸው ጋር በተጣሉ በሁለተኛው ቀን በባቡር ድሬዳዋ ተወሰዱ። ድሬደዋም ሲደርሱ ቀጥታ ያመሩት ወደ ሐረር ነበር። "ድሬደዋ ስደርስ ሐረር በሚሄድ አውብቶብስ ከዕቃ ጋር ተጭኜ ሄድሁ። ውስጥ እንዳልገባ ውስጥ መቀመጥ የተፈቀደው ለጣሊያኖች ብቻ ነበር። ሐረር ስደርስ አክስት ስለ ነበሩኝ እያጠያየቅሁ ሄድሁ። አክስቴ ሲያዩኝ አለቀሱ። <እኛ እኮ ሞተሃል ብለን ነበር> አሉና አዘኑ።"

አባባ ተስፋዬ ምንም እንኳ አክስታቸውን አግኝተው ደስ ቢሰኙም የመሥራት ፍላጎትና አቅም ስለ ነበራቸው ያለ ሥራ ቁጭ ማለትን አልፈቀዱም። በማግስቱ ጠዋት ሐረር ወዳለው እቴጌ ሆቴል ቅርንጫፍ ሄዱ። ለጀርመናዊው ኀላፊ አዲስ አበባ እቴጌ ሆቴል በቦይነት መሥራታቸውን ነገሩት <በኋላ ተመልሰህ ና!> አላቸው። አዲስ አበባ ስልክ ደውሎ በርግጥም እዚያ ሠርተው እንደ ነበረ አረጋግጠና ከሰዓት ሲመለሱ ቀጠራቸው።"

ሥራ ጀምረው ትንሽ እንደቈዩ ፋሺስት ጣሊያን ኢትዮጵያን ለቆ ወጣ። "ሆቴሉን ልዑል መኰንን ገዙትና <ራስ ሆቴል> አሉት።" የሚሉት አባባ ተስፋዬ ለሆቴሉ የምግብ ቤት ኀላፊ ሆነው ተሾሙ። እዚያ በነበሩበት ጊዜም፣ መኳንንቱ ለዕረፍትና ለመዝናናት ወደ ሆቴሉ ሲመጡ ፒያኖ ይጫወቱላቸው ነበር።

"ጃንሆይ ለጦርነቱ ድጋፍ ላደረጉ የደቡብ አፍሪካ ወታደሮች ጅጅጋ ላይ መሬት ሰጥተዋቸው ስለ ነበር፣ ይህን አስመልክቶ በራስ ሆቴል የእራት ግብዣ ተዘጋጀ። በግብዣው ላይ የእንግሊዝና የደቡብ አፍሪካ ብሔራዊ መዝሙር ማርሽ ተመታ። የእኛ ይቀጥላል ብዬ ስጠብቅ የለም። ንድድ አለኝና ለጄኔራል ዐቢይ ፒያኖ መጫወት እንደምችልና የኢትዮጵያን ሕዝብ መዝሙር መዘመር እንደምፈልግ አስታወቅሁ። ስለ ተፈቀደልኝም በዚያ ወቅት የነበረውን የኢትዮጵያ ሕዝብ መዝሙር ተጫወትሁ። ያኔ ሁሉም ብድግ ብለው ሰላምታ ሰጡ።"



በ1934 ዓ.ም በጦርነቱ ወላጆቻቸውን ያጡ ልጆች ይሰብሰቡ የሚል ትእዛዝ ከመንግሥት ተላለፈ። ይህን የመንግሥት ትእዛዝ የሰሙት አባባ ተስፋዬ ከሐረር ተመልሰው ወደ አዲስ አበባ መጡ። ይሄኔ ነው ወደ ኪነ ጥበቡ ዓለም ጥቅልል ብሎ የመግባት ዕድሉ የገጠማቸው። በ1934 ዓ.ም ግድም ዕጓለ ማውታ ተሰባስቦ በሚያድግበት ትምህርት ቤት ገብተው መማር ቀጠሉ።

በ1937 ዓ.ም የማዘጋጃ ቴአትር ቤት የቴአትር ፍላጎት ያላቸውን ሰዎች ሲያሰባስብ አባባ ተስፋዬ መሸለል፣ መፎከርና መተወን የሚችሉ መሆናቸውን የሚያውቁና የሚያደንቁ ባለ ሥልጣኖች ወደዚያ ላኳቸው። ማዘጋጃ ቤት ገብተው ለ11 ወራት ያህል ሙዚቃ፣ የቀለም ትምህርት፣ ፈረንሳይኛና እንግሊዘኛ ቋንቋ በነጻ ተማሩ። ለሚቀጥሉት 11 ወራት ያህል ደግሞ በወር 11 ብር እንደ ደመወዝ ይከፈላቸው ነበር። በ1939 ዓ.ም ገደማ ከትምህርቱ ጋር ምግብ፣ ልብስና መኝታ እንዲሰጣቸው ተፈቅዶ ነበር።

ይህ ወቅት እነ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት ብቅ ያሉበት ጊዜ በመሆኑ በኢትዮጵያ የቴአትር ታሪክ ትልቅ ስፍራ የሚሰጠው ወቅት ነበር። ይሄኔ አባባ ተስፋዬም ወደ ቴአትሩ መድረክ ብቅ አሉ። በጊዜው ሴት ተዋንያት የሉሉ በመሆኑ ብዙ ቴአትር ላይ የሴት ገጸ ባሕርይን ተላብሰው የሚጫወቱት ወንዶች ነበሩ። ከእነዚህ ወንዶች መካከል ደግሞ አባባ ተስፋዬ ቀዳሚውን ስፍራ ይይዛሉ፦ "የአቶ አፈወርቅ አዳፍሬ ቴአትር ወጣ። አርእስቱን አላስታውሰውም። ብቻ "የሞተልሽ ቀርቶ የገደለሽ በላ" የሚል ነገር አለው። በቴአትሩ ውስጥ ሴት ገጸ ባሕርይ ስለ ነበረች እንደ ሴቷ ሆኜ የተጫወትሁት እኔ ነኝ። ብዙ ትያትሮች ላይ ለምሳሌ፦ ‹ጎንደሬው ገ/ማርያም›፣ ‹ቴዎድሮስ›፣ (የግርማቸው ተ/ሐዋርያት) ‹ንጉሕ ደም›፣ ‹አፋጀሽኝ›፣ ‹መቀነቷን ትፍታ›፣ ‹ጠላ ሻጯ›፣ ‹የጠጅ ቤት አሳላፊ›... በመሳሰሉት ትያትሮች ላይ ሴት ሆኜ ሠርቻለሁ።



አባባ ተስፋዬ ሴት ሆነው ሲጫወቱ ሚካፑን (መዋቢያ መጊያጊያጋጫ) የሚሠሩት



ራሳቸው ነበሩ። መድረክ ላይ ወጥተው ሲተውኑ ፍጹም ሰው ለይቶ እንደማያውቃቸው እንዲህ በማለት ይናገራሉ፦ "እኔም የሴቶቹን አባባል፣ አረማመድ፣ አነጋገር ሁሉ ስለማውቅ እነሱኑ መስዬ እጫወት ነበር። ተደራስያኑ ሴት የለም ብለው እንዳይመስሱ ሴት አለ ብለን እንዋሽና እኔ እሠራው ነበር። ብዙ ጊዜ እንደ ሴት ሆኜ ስሠራ ካዩኝ ተመልካቾች መካከል ለትዳር የተመኙኝም ነበሩ።" አባባ ተስፋዬ ሴት ገጸ ባሕርያትን ተላብሰው የተጫወቱት ለአራት ዓመታት ያህል ነው። ከአራት ዓመታት በኋላ ግን ሰላማዊት ገ/ሥላሴ የተባለች አርቲስት ስትመጣ በወንድ ገጸ ባህርይ መተወናቸውን ቀጠሉ።

የአባባ ተስፋዬ የኪነ ጥበብ ሥራ በአገር ውስጥ ብቻ የተገደበ አልነበረም። ወደ ኮርያ ሄደው ከሥራ ባልደረቦቻቸው ጋር በመሆን አርበኞችን በፉከራና በሽለላ ይቀሰቅሱ፣ ትያትርም እየሠሩ ሰራዊቱን ያዝናኑ እንደ ነበር ያስታውሳሉ። በኮሪያ ቈይታቸውም የሃምሳ አለቅነትን ማዕረግ አግኝተዋል። በትያትር ትወና ብቃታቸውና በሙዚቃ ችሎታቸው የወቅቱ ባለ ሥልጣናት በእጅጉ ይገረሙ ነበርና ወደ ጃፓን ሄደው የጃፓንን ቴአትር ቤቶች እንዲመለከቱ ላኳቸው። ከሦስት ወራት ቈይታ በኋላም ወደ አገራቸው ተመለሱ።

ብሔራዊ ቴአትር በ1948 ዓ.ም ሲከፈት በማዘጋጃ ቤት አብረዋቸው ይሠሩ ከነበሩ ተዋንያን ጋር ወደ ብሔራዊ ቴአትር ተሸጋገሩ። እኚህ ሰው በብሔራዊ ቴአትር በተውኔት ሙያ የቆይታ ዘመናቸው በሙሉ በተሠሩ ተውኔቶች በሁሉም ላይ ተካፍለዋል ማለት ይቻላል። አባባ ተስፋዬ በብሔራዊ ቴአትር ቈይታቸው ከሰባ በላይ በሚሆኑ ትያትሮች ላይ የተሳተፉ ከመሆናቸውም በላይ፣ "ብጥልህሳ? ነው ለካ?" እና "ጠላ ሻጭዋ" የተባሉ ተውኔቶችን ጽፈዋል።

"በቴአትር ቤት ቈይታዬ ለሰዎች የሚያስቸግረውን ትያትር የምሠራው እኔ ነበርሁ። አሮጊት ጠጅ ሻጭ፣ ሲባ፣ ሰካራም ሆኜ እሠራ ነበር። አንድ ትያትር ላይ እጫዋች፣ ባለሚልና ድንክ ሆኜ ሠርቻለሁ።"



በተዋጣ ተዋናይነቱ በሕዝብ ዘንድ የሚታወቀው አርቲስት ወጋየሁ ንጋቱ ስለ አባባ ተስፋዬ የትወና ብቃት ሲናገር፣ "ጋሽ ተስፋዬ ትራጀዲም [አሳዛኝ] ኮሜዲም [አስቂኝ] ቲያትሮችን መጫወት ይችላል። ኮሜዲ በሚጫወትበት ጊዜ ዋና ችሎታው የገጸ ባሕርዩ (የድርሰተ ሰቡን) ደም፣ ሥጋና አጥንት ወስዶ የራሱ ያደርገዋል፤ ይላበሰዋልም። በዚህም የደራሲውን ሥራ አጉልቶ ያወጣዋል።" ብሎ ነበር፤ አባባ ተስፋዬም በርግጥ "ሁሉንም ዐይነት የቴአትር ዘርፎች ስጫወት ይሳካልኝ ነበር" በማለት የወጋየሁ ንጋቱን አስተያየት ያጠናክራሉ። የተሰጣቸውን ገፀ ባሕርይ ሙሉ በሙሉ ተላብሰው እንደሚጫወቱም ስለ ራሳቸው ይመሰክራሉ።

"<ኦቴሎ>፣ <የከርሞ ሰው>፣ <አስቀያሚ ልጃገረድ> በተሰኙ ቲያትሮች ላይ የተሰጡኝን ገጸ ባሕርያት ወክዬ የከወንኳቸው ግሩም ነበሩ። በተለይ <ኦቴሎ> ውስጥ ኢያጎን ሆኜ ስጫወት ብዙ ነገር ደርሶብኛል። ብዙ ሰዎች ጠልተውኝ ነበር። መኳንንቱ ሳይቀሩ <የታለ ያ ሰው ያስገደለ> እያሉ ያስፈልጉኝ ነበር። ባልና ሚስት በመኪና እኔን ለመውሰድ ተጠይፈውኝ ሁሉ ነበር። በመንገድ ሳልፍ ወይም አውቶቡስ ስጠብቅ፣ <እዩት ይሄ እርጉም መጣ!> እያሉ ይሰድቡኝና ይሸሹኝ ነበር።"

አርቲስት ጌታቸው ደባልቄ አባባ ተስፋዬን የሚያውቋቸው ከዛሬ ሀምሳ ዓመት በፊት ነው። በብዙ ትያትሮች ላይም አብረው ተውነዋል። ስለ አባባ ተስፋዬም ሲናገሩ፣ "ተስፋዬ ሳህሉን ከ1944 ዓ.ም ጀምሮ አውቀዋለሁ። ባለ ብዙ ሙያ ባለቤት ነው። ቢያንስ ቢያንስ ከሰባ በላይ የሚሆኑ ትያትሮች ላይ ሠርቷል። <ሥነ ስቅለት> ላይ ጲላጦስን ሆኖ ሲሠራ የተቀጠረለት እንደ ተዓምር ነው። <ዳዊትና ኦሪዮን> ላይም ተጫውቷል። ባላምባራስ አሸብር ገ/ሕይወት የጻፉት <የንግሥት አዜብ ጉዞ ወደ ሰሎሞን> የሚለው ትያትር ላይ ሀማ አጥማጅ ሆኖ ሠርቷል። ብሔራዊ ቴአትር መጥተው የነበሩ ጀርመኖች እስክንለያይ ድረስ የሚጠሩት <ፊሸር> እያሉ ነበር። <ኦቴሎ> ላይ ኢያጎን ሆኖ ሲሠራ ብዙ ተመልካቾች፣ <ከፋቱንና ጭካኔውን በድምፁ



ጀሮ



ብቻ ሳይሆን በዐይኑም ጭምር ተናገረለት> ብለው የመሰከሩለት ሰው ነው። ጸጋዬ ገ/መድኅንም በጣም አድንቆታል።"

አባባ ተስፋዬ ከሚሠሯቸው ትያትሮች በተጨማሪ በተለያዩ መድረኮችና በቴሌቪዥን በሚያቀርቧቸው የምትሃት (የማጂክ) ትርኢቶች ይታወቃሉ። ስለ ምትሃት ችሎታቸው የሚከተለውን ይላሉ፤ "ምትሃቱን ያሠለጠነኝ በጃንሆይ ፈቃድ እንድ እሥራኤላዊ ነው። ኮርያም አይቼ ስለ ነበር ትንሽ ትንሽ እችል ነበር። ያንን ሳሳየው ደስ ብሎት አስተማረኝ። በጅምናስቲክ የሚሠሩትን ፣በገመድ ላይ መሄድና አክሮባት አሠለጠነን። ስመረቅ ጃንሆይ ሽልማት ሲሰጡኝ፣ <አስተምርበት እንጂ እንዳታታልልበት!> አሉኝ"፤ "ይሁን እንጂ በዚህ ጥበቤ ያተረፍሁት አድናቆትንና ከበሬታን ሳይሆን በሰዎች ዘንድ መጠላትን ነው" የሚሉት አባባ ተስፋዬ "ሰዉ ዕውቀት ስለማይመስለው አስማተኛው በማለት ይጠላኝ ነበር።" ሲሉ በሐሳብ ወደ ኋላ ሄደው ያስታውሳሉ።

ከትያትር ሙያቸው በተጨማሪ አባባ ተስፋዬ በብዙኃኑ ዘንድ የሚታወቁት በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን፣ በልጆች ፕሮግራም ላይ በሚያቀርቡት አስተማሪ፣ መካሪና አዝናኝ በሆኑት ተረቶቻቸው ነው። ለ42 ዓመታት በዚህ ፕሮግራም ላይ ያገለገሉት አባባ ተስፋዬ በፕሮግራሙ ብዙ ኢትዮጵያውያን ልጆችን እንዳሳደጉበት ይናገራሉ። ወደ እዚህ ሙያ እንዴት እንደ ገቡ ሲናገሩም ፦ "በ1957 ዓ.ም የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ሲቋቋም ሁሉ ነገር ተዘጋጀ። ኮንትራቱን የያዘው አንድ እንግሊዛዊ ነበር። ያኔ የልጆች ፕሮግራም አልነበረምና ሄጄ ለሳሙኤል ፈረንጅ ነገርኳቸው። <አይ ያንተ ነገር!> አሉና እውነትም ኮንትራቱን ሲያዩት የልጆች ፕሮግራም የለም። እንግሊዛዊውን ሲጠይቁት <ሰው አላችሁ ወይ?> ብሎ ጠየቀ። እኔ እንድሠራ ሳሙኤል ለእንግሊዛዊው ጠቈሙት። እስኪ ግባና አሳየኝ ሲለኝ የነበረኝን አስቂኝ ማስክ ይዤ ወጥቼ ያን አጥልቄ አሳየሁት። ባሳየሁት ነገር ተገረመና፣ <አንተ እዚህ ምን ትሠራለህ?> አለኝ። <አገሬን ስለምወድ ውጪ ወጥቼ መቅረት አልፈልግም።



ጀሮፅ

የአገሬ ሰው መቼ ጠግበኝና እንዲህ ትለኛለህ?> አልኩት። ኅዳር 1 ቀን 1957 ዓ.ም <ጤና ይስጥልኝ ልጆች የዛሬ አበባዎች የነገ ፍሬዎች!> ብዬ በቴሌቪዥን ቀረብኩ።"

"ለልጅ ልዩ ፍቅር አለኝ። መንገድ ላይ እንኳ መክሬ፣ ተቈጥቼ ነው የማልፈው።" የሚሉት አባባ ተስፋዬ ፕሮግራማቸውን ወላጆች ሳይቀሩ እንደሚወዱት ይናገራሉ። "በየአጋጣሚው፣ <እኛ በእርስዎ ምክር አደግን፣ ልጆቻችንንም በእርስዎ ምክር አሳድገናል> የሚሉኝ ብዙ ናቸው።"

አባባ ተስፋዬ ሥራቸው ያስገኘላቸው የሕዝብ ፍቅር እንጂ የገንዘብ ሀብት እንዳልሆነ ደጋግመው ይናገራሉ። "ቴሌቪዥን ስገባ መጀመሪያ እንግሊዙ ጥሩ ገንዘብ ይከፍለኝ ነበር (በወር 175 ብር ነበር የሚከፍለኝ)። በኋላ ግርማቸው ተክለ ሐዋርያት፣ <ተስፋዬ አሄሄሄ! ወፍ እንዳገሯ ነው የምትጮኸው፤ ...እንደ ፈረንጅ አይደለም የምንከፍልህ፤ ሰባ ብር ይበቃሃል> አሉኝ። በፕሮግራም ስለ ሆነ ጥሩ ነበር። ያችንም በኋላ ደርግ ሲመጣ 50 ብር አደረጋት። እሱም ጥሩ ነበረ። ግን ሲሄድ ሃያ አምስት ብር አድርጓት ሄደ። አሁንም ሃያ አምስት ብር ነው። በሃያ አምስት ብሬም ቅር አላለኝም። እኔ የምፈልገው በልጆች አእምሮ ውስጥ እንድገባ ነው። ሕግ እንዲማሩ፣ ሲያድጉ እንዳያጠፉ፣ ጉበዝ ተማሪ እንዲሆኑ ነበር የምፈልገው፤ ተረቶቼ ሥነ ምግባርን ነበር የሚያስተምሩት።"

አባባ ተስፋዬ ለረዥም ዓመታት በቴሌቪዥን ለልጆች ተረትን ከመተረታቸው በተጨማሪ በኪነ ጥበቡ ዘርፍ ላበረከቱት አስተዋፅኦ ከተለያዩ መንግሥታዊና መንግሥታዊ ካልሆኑ ድርጅቶች በዛ ያሉ የምስክር ወረቀቶችንና ሽልማቶችን ተቀብለዋል። ከእነዚህ መካከል የኢትዮጵያ የኪነ ጥበባትና የመገናኛ ብዙኃን ሽልማት ድርጅት በቴአትር ዘርፍ በተዋናይነት የ1991 ዓ.ም የሕይወት ዘመን ተሸላሚ ያደረጋቸው በዋናነት የሚጠቀስ ነው።






አባባ ተስፋዬ ከኪነ ጥበብ ሥራ ጋር በተያያዘ ወደ ግብፅ፣ ኮርያ፣ ጃፓን፣ ጀርመን፣ ሱዳንና ወደ ሌሎችም አገሮች ሄደው መጥተዋል። "ከውጪ ስመጣ ሁል ጊዜ ልቅሶ ይይዘኛል።" የሚሉት አባባ ተስፋዬ ከኮርያ እስከ ጃፓንና ጀርመን ድረስ ሄደው ሲመለሱ በእጅጉ የሚያሳስባቸው ያገራቸው አለማደግ እንደ ሆነ ይናገራሉ፤ "መቼ ነው አገሬ አድጋ የማያት! መቼ ነው ከግር ቤት የምንወጣው! እያልኩ እጸጸታለሁ። ቤቶቹ በቆርቆሮ ሲተኩ ደግሞ መቼ ነው? መንገድ የሚሠራው? ሥርዓት የምንማረውስ መቼ ነው በማለት ይቈጨኝ ነበር። በፊት አገሬ መንገድ ስለሌላት በጣም እናደድ ነበር። አሁን ግን እየተሠራ በመሆኑ ደስ እያለኝ ነው።"

አባባ ተስፋዬ ለልጆች የሚሆኑ አራት የተረት መጻሕፍት ጽፈዋል። ከመድረክ ላይ የተቀዱ ሁለት ካሴቶች አሏቸው። "ከብሔራዊ ቴአትር ጡረታ ከወጣሁ 24 ዓመት ሆኖኛል።" የሚሉት አባባ ተስፋዬ "አራት የተረት መጽሐፎቼን፣ በቴሌቪዥን መስኮት የምታይበት ፎቶ ያለበትን ቲሸርትና ካሴቱን በትልልቅ ሱቅና ቡና ቤት፣ መንገድም ላይ እያዞርኩ በመሸጥ ራሴን እደጉማለሁ" ይላሉ። ከዚህ በተጨማሪ አባባ ተስፋዬ ከብሔራዊ ቴአትር 300 ብር ጡረታ ያገኛሉ።

"የወለድኳቸው ሁለት ልጆች ቢሆኑም አንዱ ልጄ ሞቷል" በማለት የሚናገሩት አባባ ተስፋዬ ከቤተ ሰባቸው ጋር የጠበቀ ግንኙነት እንዳላቸው ይገልጻሉ። ስለሆነም ከአምስት የልጅ ልጆቻቸውና አራት የእኅታቸው የልጅ ልጆች ጋር እህታቸውንም ጨምሮ ከ 14 ቤተ ሰብ ጋር አብረው እንደሚኖሩም አያይዘው ገልጸዋል።

ባለቤታቸው ከዚህ ዓለም በሞት ከመለየታቸው በፊት በሥራቸው ላይ የነበራቸውን አዎንታዊ ተጽዕኖ እንዲህ በማለት ይገልጹታል፦ "ባለቤቴ ሥራዬን ትወድልኝ ነበር። በርታ ትለኝ ነበር። ስበሳጭ፣ ስናደድ የምነግራት ለእርሷ ነበር፤ <ግዴለም ተስፋ ቻለውና አሳልፈው> ትለኝ ነበር። ከ48 ዓመት የትዳር ሕይወት በኋላ የዛሬ ሦስት ዓመት ሞታብኛለች።"



አንዱ ልጃቸው ገና ትንሽ ሳለ ትያትር እንደ ሠራ የሚያስታውሱት አባባ ተስፋዬ ኮንጎ ይኖር የነበረው ትልቁ ልጃቸው ሙዚቃ መጫወት ይችል እንደ ነበር ገልጸዋል። የልጃቸው ልጅ ከአባቱ ጋር ሆኖ የሙዚቃ ክሊፕ ቤታቸው ውስጥ ባለው ስቱድዮ እየሠራ ሲሆን፣ እርሳቸውም በዋና ገጸ ባህርይነት የሚተውኑበት ፊልም ለመሥራት በዝግጅት ላይ መሆናቸውን ተናግረዋል።

አቶ ተፈራ ተስፋዬ ይባላሉ። የአባባ ተስፋዬ ሁለተኛ ልጅ ናቸው። "የአራት ዓመት ልጅ ከነበርሁበት ጊዜ አንሥቶ እስከ 1970ዎቹ ድረስ ከአባቴ ጋር አብሬ እየሄድሁ ቴአትር እመለከት ነበር።" የሚሉት አቶ ተፈራ፣ "ቤት ውስጥ ሲለማመድ አይ ነበር። ግን አልረዳውም ነበር። የማተኩረው ትምህርቴ ላይ ነበር። ምግብ እየተበላ ዝም ብለን እየተጫወትን ድንገት ትዝ ሲለው ጮኾ ያጠናውን ቴአትር በቃሉ ይወጣው ነበር። ብዙ የሚያስቸግረው የጸጋዬ ገ/መድኅን ቴአትር ነው። ቃላቱ ከበድ ከበድ ያሉ ስለ ነበሩ እየበላም ሲለማመድ አየው ነበር።"

አቶ ተፈራ የስድስት ዓመት ልጅ እያሉ «ቴዎድሮስ» ትያትር ላይ ሚኒሊክን ሆነው የተጫወቱ ሲሆን ትያትሩ ላይ አባታቸው አባባ ተስፋዬ ራስ መኮንንን ሆነው እንደ ሠሩ ያስታውሳሉ። አጫጭር የቴሌቪዥን ድራማዎች ላይም መተወናቸውንም አያይዘው ገልጸዋል።

ወ/ሮ ወይንሸት ተሾመ የአባባ ተስፋዬ ልጅ (የአቶ ተፈራ ተስፋዬ) ባለቤት ስትሆን እሷም ስለ አባባ ተስፋዬ የምትለው አላት፤ ‹አባባ ተስፋዬ የእኛ ብቻ ሳይሆኑ የኢትዮጵያ ሕዝብም አባት ናቸው። ልጃቸውን በማግባቴ ለ 19 ዓመታት ያህል አውቃቸዋለሁ። ለ 15 ዓመታት ደግሞ አብረን ኖረናል። ጥሩ አባት ናቸው። ከውጪ ሲመጡ የቤት ሰዉ አባል ጐድሎ ማየት አይፈልጉም። ገና ሲገቡ ምሳ በልታችኋል ወይ ይላሉ። ሌላ ቦታ ከተጋበዙ ደውለው ይናገራሉ። ዘመዶቻቸውን ሰብስበው ይይዛሉ።"





ዛሬ አባባ ተስፋዬ 84 ዓመታቸው ነው። አሁን ግን ለ42 ዓመታት ባገለገሉበት የኢትዮጵያ ቴሌቪዥን የሥራ መስክ ላይ አይደሉም። ኀይሉ ጸጋዬ ስለ እኚህ ታላቅ የኪነ ጥበብ ሰው የሚከተለውን በጽሑፉ አስፍሯል፦ "ልብ በሉ! 40 ዓመታት! በእንደዚህ ዓይነት ኪነ ጥበብ ውስጥ ለረዥም ዘመናት ከቆየ ሰው የሚገኘው ልምድ፣ ዕውቀት፣ ትዝታ፣... በምን ሊለካ ይችላል? ...ትራጀዲ፣ ኮሜዲ፣...የሰዉቸውን በትክክል የሚጫወቱ ከዚህ በተጨማሪ ሙዚቀኛ፣ ምትሐተኛ (ማጂሺያን)፣ ዘፋኝ፣ የሕፃናት አስተማሪ፣ የውዝዋዜ አሠልጣኝና አስተዋዋቂም ጭምር ናቸው። ይገርማል! አንድ ሰው እንዴት [የዚህ ሁሉ] ኪነ ጥበብ ዘርፍ ባለ ሙያ ሊሆን ይችላል!?"

## <u>መወድስ</u>

**አባባ ተስፋዬ መች አንድ ሰው ናቸው**
**ዘርፈ ብዙ ጥበብ እግዜር ያደላቸው**
**ወታደር ተዋናይ ሙዚቀኛ ሆነው**
**በተረት ቁም ነገር ትውልድ አስተምረው**
**በአባት በልጆች ልብ ይኖራሉ ደምቀው**



## ትምህርተ ውልብታ

በቍርጠኛ አቋም ሥራን ሳይመርጡ መሥራት፤

ነገሮችን እንደ አመጣጣቸው የማስተናገድ ጸጋ ደመወዛቸው ቢያሽቆለቁልም ወደ ኋላ አለማለታቸው፤

ጥቅሙ የሚታወቀው በኋላ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ቢሆንም ሌሎች ቋንቋዎችን ለማወቅ ጥረት ማድረግ

የሰው ድካምና ጥረት ሁሉ በገንዘብ ላይተረጎም ይችል ይሆናል፤ ቢሆንም በሰዎች ሕይወት ለውጥ ማምጣት ከቻለ ትልቁ ትርፍ ያ ነው።

### የውልብታ ምንጭ

የካቲት መጽሔት፣ ከነይሉ ጸጋዬ፣ "እንጋፋው ከያኒ"፣ ጥር፣ 1979 ዓ.ም፤ ገጽ 19 - 20

ማለዳ መጽሔት፣ "የተረት አባት አባባ ተስፋዬ"፣ የጸሓፊው ስም ያልተጠቀሰ፣ ቅጽ 2፣ ቍጥር 7 ጥርና የካቲት 1999 ዓ.ም፤ ገጽ 7-8 9

ከአባባ ተስፋዬ ሳህሉ ኤጀርሳ ጋር የተደረገ ቃለ ምልልስ፣ የካቲት 1999 ዓ.ም።

Ababa Tesfay`s Great Journey, *ethiomirror.com.*



## የአንባቢው የግል ማስታወሻ





# ፲፩



ዓለማየሁ አበበ

1916–

በምድር እንደ ጉንዳን ታተረ

በሰማይ እንደ አሞራ በረረ

አንዲት አፍሪካዊት አገር ሃያ ዓመት ባልሞላ ጊዜ ውስጥ ከምንም ተነሥታ በወቅቱ እጅግ ዘመናዊ ወደ ሆነው የጄት ቴክኖሎጂ ውስጥ ልትገባ ስትል ለአፍሪካዊያን ታላቅ ኩራት ሲሆን ምዕራባውያን አገሮችን ደግሞ ማስደንገጡ አንቀረም።

የባልና ሚስት ፍቺ ምክንያቱ ምንም ይሁን ምን፣ ፍዳው ወደ ልጆች መሸጋገሩ አይቀርም። የባላንባራስ አበበ ደስታ ቀዊ ትዳርም ይህ ዕጣ ወደቀበትና ጉልቻው መፍረሱ ቍርጡ ሲታወቅ፣ ከሚስታቸው ከወይዘሮ ጥሩነሽ ጋር ልጆቻቸውን ተከፋፈሉ። የካቲት 16 ቀን 1916 ዓ ም የተወለደውና በመወለዱም ዓለም እንደ ታየ ታስቦ፣ ዓለማየሁ ያሉት የአምስት ዓመት ልጃቸው በአባት ሙጥኝታ አሳቸው ዘንድ እንዲኖር ተወሰነ።

ዓለማየሁ አንዴ በጨርጨር አውራጃ በአባቱ ቤት፣ አንዴ ደግሞ በባቢሌ በአያቱ በግራዝማች ደስታ ቀዊ ቤት እየተመላለሰ ለሁለት ዓመት ያህል ቈይቷል። ስባት ዓመት ሲሞላው ወደ ሐረር ከተማ ዘመድ ጥየቃ በሄደበት ዘመናዊ ትምህርት እንዲማር ተወሰነና እዚያው ቀረ። ይሁን እንጂ በየክረምቱ ቤተ ሰብ ለመጠየቅ ወደ ባቢሌ መምጣቱ ግድ ነበር። ከእነዚህ ክረምቶች በአንዱ የዓለማየሁን የወደ ፊት ሕይወት የሚወስን አንድ ክሥተት በሰማይ ላይ ተገለጠ። ሰው ሠራሹን አሞራ የጅጅጋን ሰማይ ሰንጥቆ ሲበር አየ። በዚህ ጊዜ ዓለማየሁ አውሮፕላን የማብረር ብርቱ ፍላጎትና ምኞት አደረበት።

የዓለማየሁ አሳዳጊ በሐረር ከተማ የታወቁና የተከበሩ የካቶሊክ እምነት ተከታይ ስለ ነበሩ፣ ዓለማየሁ በካቶሊክ ሚሲዮን ገብቶ መንፈሳዊና የቀለም ትምህርት የመከታተል ዕድል አገኘ። ከዚህ ቈይታው የተነሣ አዳጊው ዓለማየሁም የካቶሊክን ሃይማኖት ተቀበለ። የዲቁናን ትምህርትና ሥርዓት ጠንቅቆ በማወቅም ገና በአፍላነቱ መንፈሳዊ አገልግሎትን መስጠት ጀመረ።

ይሁን እንጂ እያደር ለአገልግሎት ከቤተ ክርስቲያን ውጪ በተደጋጋሚ በሚመላለስበት በጣሊያኖች ካምፕ፣ ንቃቱን የተመለከተ አንድ ጣሊያን ካምፕ ውስጥ ሥራ እንዲሠራ ቀጠረው። በዚህም ምክንያት ከትምህርቱ ይልቅ ወደ ሥራው ዓለም አዘነበለ። በጣልያኖች ካምፕ ውስጥ ልብስ በማጠብ፤ በመላላክና በሾፌርነት ሲያገለግል ከቈየ በኋላ አሁንም ከአንድ ጣልያናዊ ጋር የአስተርጓሚነትና





የጽሕፈት ሥራ ለመሥራት ካምፑን ለቆ ወደ ሐረር ከተማ ሄደ። ከዚያም በሕንጻ ሥራ ግንባታ ላይ በኀላፊነት ሲሠራ ቈየ። ከሌሎች የጣሊያን ቀጣሪዎች ጋርም ወደ ድሬድዋ ሄዶ በተለያዩ ቦታዎች በግል ሲሠራ ከቈየ በኋላ በመጨረሻ የመንግሥት ተቀጣሪ ሆነ። ይህም ለወጣት ዓለማየሁ የቅድመ ጣሊያን ወረራና የጣሊያን ወረራ ጊዜ ራስን የመቻል የኑሮ ፍልሚያ አዲስ ምእራፍን ከፈተ።

ድሬዳዋ ከመምጣቱ በፊት ገና በለጋ ዕድሜው የራሱን ምግብ አብስሎ መብላት መቻሉ፣ በቤተ ክህነት በዲቁና ማገልገሉ፣ በጣሊያኖች መኖሪያ ቤቶች በቤት ሠራተኛነት፣ በሾፌር ረዳትነትና በሾፌርነት መሥራቱ፣ በግንባታ ሥራ ተቈጣጣሪነት፣ በሬስቶራንት ሠራተኛነት፣ ድሬዳዋ ከመጣ በኋላም በተምኔክ ትራንዚት መልእክተኛነት፣ በፖስታ ቤት ቴሌግራም ሠራተኛነት፣ በባቡር ሐዲድ ሥራ ቡሎን አቀባይነት፣ በጨርቃ ጨርቅ ፋብሪካ ሠራተኛነት መሥራቱ የሥራን ክቡርነት ከሰው አይቶ ሳይሆን በራሱ ጥረትና በገዛ ላቡ ተምሮት እንዲያድግ አድርጎታል።

በዚህኛው የሕይወት ትግል ምዕራፍ ውስጥ እያለ በኢትዮጵያ የነጻነት ሎሩ ሊፈነጥቅ ጀመረ። ተወልዶ ባደገበት የምሥራቅ ኢትዮጵያ የአየር ክልል በጣሊያንና በእንግሊዝ አውሮፕላኖች መካከል የነበረው የአየር ላይ ፍልሚያ ለዓለማየሁ ወደ ፊት የሕይወቱ ትግል መሬት ለመሬት ብቻ ሳይሆን፣ በአየር ላይም እንደሚሆን እያመላከተው ነበር።

ፋሽት ከኢትዮጵያ በግድ ተገፍትሮ ሲወጣና ወረራው ሲያበቃ፤ የወጣት ዓለማየሁ የለጋ ዕድሜ ትግል ግን ቀጠለ። ከነጻነት በኋላ የትምህርቱን የመቀጠልም ሆነ የተሻለ ሥራ የማግኘቱ ጉዳይ እየከበደበት ሄደ። ከዚህም የተነሣ ትምህርቱን ለመቀጠል ሲወስን በወቅቱ የነበረው ብቸኛ አማራጭ ወደ አዲስ አዲስ አበባ በመምጣትና የመንግሥት አዳሪ ትምህርት ቤት መግባት ነበር። ወዳጅ ዘመድ ባይኖረውም ወደ



አዲስ አበባ መምጣት ግድ ሆነበት ።

የድሬዳዋ ከተማ ቈይታውና ቀደም ብሎ ያደረገው አጭር የአዲስ አበባ ጕብኝት እንደ ቅድመ ዝግጅት ቢጠቅመውም፣ ለትምህርቱ ሲል ከሐረር አንስቶ እስከ አዲስ አበባ ያሉትን የመንግሥት መሥሪያ ቤት ቢሮዎች ማሠሡና ደጅ መጥናቱ ግን ለዓለማየሁ ሌላ እልህ አስጨራሽ ትግል ነበር። አስቀድሞ በትዕግሥት ዝቅ ማለትንና ከጊዜ በኋላ ግን የሚፈለገውን በማግኘት ከፍ ማለት እንደሚቻል ከኑሮው የተማረው ወጣት ዓለማየሁ፣ ይህ ደጅ ጥናት ተስፋ እንዲቈርጥ አላደረገውም። ከሐረር የመንግሥት ባለ ሥልጣኖች የተሰጠውን የአባቱን በወልወል ጦርነት መሠዋት የሚገልጽ መረጃ ለአዲስ አበባ የትምህርት ሚኒስቴር ሹማምት በማቅረብ፣ ደጅ ጥናቱንና እንግልቱን ሁሉ አልፎ ጉለሌ የሚገኘው የባላባት ትምህርት ቤት (በአሁኑ መጠሪያው መድኀኔ ዓለም ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት) ተማሪ ለመሆን በቃ። ይህ ሲሆን ዕድሜው አሥራ ስምንት ዓመት ነው። ተወልዶ ካደገበት ቈላማ የምሥራቅ ኢትዮጵያ ግዛት የመጣው ዓለማየሁ ጉለሌ በደጋማው የአዲስ አበባ ክፍል በመኖር ውጪውን ቢበርደውም፣ ውስጡ ግን ለትምህርት እንደ ጋለ ትግሉን ቀጠለ። በጊዜው ራሱን በአማርኛ፣ በኦሮምኛ፣ በጣሊያንኛ፣ በፈረንሳይኛና በዐረብኛ ቋንቋዎች በደንብ መግለጽ የሚችለው ዓለማየሁ በትምህርት ቤቱ የሚሰጠውን ትምህርት በሚገባ ስላጠናቀቀና አጥጋቢ ውጤት ካመጡት ተማሪዎችም አንዱ ስለ ነበረ፣ አዲስ ወደ ተከፈተው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ገባ። ከልጅነቱ ጀምሮ ትጉህ ሠራተኛ የነበረው ዓለማየሁ ትጉህ ተማሪነቱን ደግሞ ለራሱና ለሚከታተሉት ሁሉ አስመሰከረ። በዚህም ሌላ ታላቅ የሕይወቱ ታሪክ የሚጀምርበት አዲስ ምዕራፍ ተከፈተ።



ይሁን እንጂ የዓለማየሁ ርእይ በባቢሌ ሰማይ ከሰው ሠራሹ አሞራ ጋር እንደ ተንጠለጠለች ናት። በወቅቱም ከመድኀኔ ዓለም ትምህርት ቤት ግቢ ሁለት ተማሪዎች ቀን ቀን



የበረራ ትምህርት እየተማሩ ማታ ብቻ ለአዳር መምጣታቸውን ቢሰማም፣ የግድ ሆኖበት በጊዜው እንደ ብርቅ ወደ ሚታየውና የመጀመሪያው ወደ ሆነው የመምህራን ማሠልጠኛ ተቋም ገባ እንጂ የሕይወቱ ጥሪ ጥቍሩ ሠሌዳና ጠመኔው እንዳልሆነ ገብቶት ነበር።

አውሮፕላን የማብረር ጕዳይ ከዓለማየሁ ልብ ውስጥ ስላልጠፋ መረጃዎችን ሲያጠያይቅ የቅጥሩ ምንጭ የሚገኘው ገንዘብ ሚኒስቴር ውስጥ፣ የቅጥሩም መመዘኛ የእንግሊዘኛ ቋንቋና የሂሣብ ችሎታ መሆኑን ተረዳ። ጊዜ ሳያባክን ከሌሎች ተማሪዎች ጋር በመሆን ወደ ገንዘብ ሚኒስቴር መሥሪያ ቤት ሄደ። በጊዜው ምክትል ሚኒስቴር ወደ ነበሩት ወደ ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ ቀርቦ ዐብረውት ከሄዱት ታማሪዎች ጋር አንዳንድ መመዘኛዎችና ጥያቄዎች ከቀረበላቸው በኋላ፣ መልካቸውንና አቋማቸውንም በማየት ዓለማየሁና ሌሎች ሦስት ተማሪዎች ተመርጠው ወደ ሲቪል አቪየሽን ሄደው እንዲያመለክቱ ተነገራቸው።

በዚያን ወቅት የአቪየሽን ትምህርት ቤት የሚገኘው ከአዲስ አበባ ወደ ሰበታ መውጫ መንገድ በኩል አሮጌው አውሮፕላን ማረፊያ በሚባለው ስፍራ ነበር። የመጀመሪያው የአየር ኀይል የአቪየሽን ትምህርት ቤት የተቋቋመውም በዚያ ግቢ ውስጥ ነበር። ከጥቂት ተማሪዎች ጋር በመሆን በጊዜው በኰሎኔል ጆን ሮቢንሰንና ሌላ ሦስት አፍሪካ አሜሪካውያን አስተማሪዎች አማካኝነት «የበረራ ትምህርት» ተጀመረ። ይሁን እንጂ የዓለማየሁ የአቪየሽን ትምህርት ቤት የመጀመሪያ ዓመት ቈይታ እጅግ ፈታኝ ነበር።

ምንም እንኳ የአቪየሽን ትምህርት ቤት የተቋቋመው ከድል በኋላ ለኢትዮጵያ የበረራ ትምህርት ቤት እንደሚያስፈልግ ታምኖበት ቢሆንም፣ ሠልጣኞቹ ግን በዘመድ አዝማድ የተሰባሰቡ፣ ዕድሜአቸውና የትምህርት ችሎታቸው ለበረራው ሥልጠና የማይመጥን ከመሆኑ የተነሣ፣ አሠልጣኞችን እጅግ ያደከመና ያሰለቸ ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር።



ከዚህ በተጨማሪም የንድፈ ሐሳቡ ሥልጠና በትምህርት ላልገፉት ተማሪዎች ስላስቸገረ፣ ከአሮጌ አውሮፕላን ማረፊያ በዋናው ፖስታ ቤት በስተ ጀርባ ወዳለውና በወቅቱ «ኦርማ ጋራዥ» ተብሎ ይጠራ ወደ ነበረው ትልቅ የትልልቅና የአነስተኛ መኪናዎች ማደሻ ስፍራ ተማሪዎችን በማመላለስ የተግባር ሥልጠና ማካሔድ የግድ ነበር።

የኦርማ ጋራዥ ምልልስ እ.ኤ.አ ሕዳር 1944 ዓ.ም. በሁለት የአሜርካን ሴስና አውሮፕላኖች መምጣት ቢያበቃም ለእነ ዕጬ መኰንን ዓለማየሁ ግን ይህ ከስተት ያመጣው ለውጥ አልነበረም። ይልቁንም ኢትዮጵያውያን ተማሪዎች አውሮፕላኖችን በአቪየሽን ግቢ ውስጥ ከማጠብና ከማጽዳት፣ የተለመደ ስፖርት ከመሥራትና የቤዝቦል ሜዳ ሣር ከማጨድ የዘለለ ዕድል ፈንታ አልነበራቸውም።

የአቪየሽን ትምህርት ቤቱ ሁኔታ በአስተማሪና በአውሮፕላን ዕጥረት የተነሣ ችግር ላይ ቢወድቅም ለኢትዮጵያ ፍቅር የነበራቸው ቮን ሮዘን የተባሉት ስዊድናዊ ሦስት አሠልጣኞችና አንድ አውሮፕላን ይዘው መጡ። ይህ ርምጃ መልካም ዕድል ፈጥሮ ዕጬ መኰንን ዓለማየሁ ቮንሮዘን ካመጧቸው አሠልጣኞች አንዱ በሆኑት በካፕቴን ስቬንሰን አማካኝነት ሊሠለጥን በቃ። ባቢሌ መሬት ላይ ሆኖ ሽቅብ ሰማይን በማንጋጠጥ ያየው ትንሹ ዓለማየሁ እ.ኤ.አ ሰኔ 1946 ዓ.ም የመጀመሪያ አሐዳዊ በረራውን *(solo flight)* በማድረግ ከሰማይ ሆኖ የኢትዮጵያን ምድር ቁልቁል መቃኘት የቻለ ፓይለት ሆነ።

የበረራን ሀ ሁ በዚህ ሁኔታ የጀመረው ዓለማየሁ፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ ኢትዮጵያ አምስት ስዊድን ሠራሽ የሆኑ ሳፊር አውሮፕላኖችን ስትገዛ ከሌሎች አብራሪ ጓደኞቹ ጋር በመሆን አንዳንድ አውሮፕላን በነፍስ ወከፍ እያበረሩ ከስዊድን ኢትዮጵያ አድርሰዋል። በርካታ የአፍሪካ አገሮች የነጻነትን ሕልም በሚያልሙበት በሁለተኛው ዓለም ጦርነት መባቻ አምስት ጥቋቊር አሞሮች የአፍሪካንና የአውሮፓን አየር እየሰነጠቁ ማለፋቸው ሲታሰብ፣ ለአፍሪካ ብሎም





ለኢትዮጵያ የታሪክ ኩራት አሻራን የተወ እንደ ሆነ ልብ ይሏል።

እነዚህ አውሮፕላኖች የስዊድን አየር ኀይል የተገለገለባቸው ቢ17 የተባሉ ቦምብ ጣይ አውሮፕላኖች (ዳይቭ-ቦምበር) ሲሆኑ ተገዝተው የመጡትም አየር ኃይሉ ወደ ደብረ ዘይት ከተዛወረ በኋላ ነው። ቀስ በቀስ ዓለማየሁ ከባለ አንድ ሞተሩ ሳፊር፣ ወደ ባለ ሁለት ሞተሩ ሴስና፣ ከዚያም በቢ17 እና በኤል 5 አውሮፕላኖች በተደረጉት በረራዎች ከሠለጡትና ከአበረሩት መካከል አንዱና ዋነኛው ለመሆን በቃ። ከዚህ በኋላ በታኅሣሥ 1942 ዓ.ም አፄ ኃይለ ሥላሴ በተገኙበት የምክትል መቶ አለቅነት ማዕረግና በውጤቱም የተለየ ሽልማት አገኘ።

ከፍ በተባለ ቊጥር ተግዳሮቱም የዚያኑ ያህል ጠንካራ እንደሚሆነው ሁሉ፣ ከኢትዮጵያውያን ፓይለቶች የመጀመሪያው ዓለም ዐቀፍ በረራ በኋላ በምክትል የመቶ አለቃ ዓለማየሁ የሙያ ሕይወት ውስጥ ብዙ ውጣ ውረዶች ዐለፉ። ሩቅ አሳቢው ዓለማየሁ ከተዋጊ አውሮፕላን አብራሪነት ወደ በረራ አስተማሪነት አዘነበለ። በዚህም የአስተማሪነቱ ጅማሬ ወቅት ለተጨማሪ ሥልጠና እንግሊዝ አገር ለመሄድ በዝግጅት ላይ እያለ በተፈጠረ አተካራ ከእንግሊዝ ጕዞ ቀረ። በዚህ አጋጣሚ የዓለማየሁ የእንግሊዝ በር ሲዘጋ የኢትዮጵያ አየር መንገድ በር ተከፈተለት። ከአዛገሮቹ ጋር በመስማማትም ከሌሎች አራት የረዥም ጊዜ አጋሮቹ ጋር በመሆን ከበራሪነቱ በስተቀር፣ ኀላፊነቱና የሥራ ግቡ ፈጽሞ የተለየ ወደ ሆነው ወደ ኢትዮጵያ አየር መንገድ ተዛወረ። ይህ የሆነው እ.ኤ.አ 1951ዓ.ም ነው። ዓለማየሁ አየር መንገዱን ተቀላቅሎ የክፍል ትምህርቱንና ምስለ በረራ ሥልጠናውን በካይሮ አደረገ። ከዚህ በኋላ አየር መንገዱን ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት በፊት እ.ኤ.አ በ1930ዎቹ ዓመታት በተሠሩ ዳኮታ ዲሲ 3 አውሮፕላኖች ወደ ዘመናዊነት ለማሸጋገርና ትርፋማ ለማድረግ ስላልተቻለ፣ ኮንቬየር 240 የተባሉት ምቾትና ፍጥነት ያላቸው አውሮፕላኖች ተገዙ። ዓለማየሁም በእነዚህ አውሮፕላኖች በረዳት



አብራሪነት ተሰማራ። ከሁለት ዓመት በላይ በአዲሶቹና በነባሮቹ አውሮፕላኖች በሰጠው የበረራ አገልግሎት ውጤታማ የበረራ ችሎታ ማረጋገጫና ምስጋና ቢሰጠውም፣ የአየር መንገዱ አስተዳደር በአሜሪካኖች ከመያዙ የተነሣ ሊያገኝ የተገባው ሙያዊ እድገት እጅግ እየተጓታ መጣ።

በአጠቃላይ በጊዜው አስተዳደሩን ይዘውት በነበሩት አሜርካኖችና በኢትዮጵያውያን አብራሪዎች መካከል የመስማማቱ ነገር እጅግ አዳጋች እየሆነ ሄደ። ከዚህም የተነሣ የሙያና የዘረኝነት ፍልሚያው ቀጥሎ ነገሩ ከአየር መንገድ ቦርድ ዘንድ ቢደርስም፣ ወሳኞቹ ራሳቸው አሜሪካውያኑ ናቸውና ከእነርሱ ውሳኔ መውጣት አልተቻለም። በተጨማሪም በወቅቱ በአየር መንገዱ አብዛኛዎቹ ተጠቃሚዎች የውጭ አገር ዜጎች በተለይም ነጮች ስለ ነበሩ በጥቁሮች እምነት አልነበራቸውም። የዚህም ሁሉ ዘረኝነት ቀዳሚ ተጠቂ ዓለማየሁ ነበር።

የዓለማየሁ የበረራ ልምድና ያበረረባቸው ዓመታት ለካፒቴንነት ብቁ ቢያደርጉትም፣ በጊዜው ውሳኔ የሚሰጡት አሜሪካውያን የኢትዮጵያውያኑን ዕድገት የሚያዘገዩበትን ስልት በመቀየስ፣ ለካፕቴንነት ብቁ አይደለም በሚል ተጨማሪ ሁለት ዓመታት አዘገዩት። የሆነው ሆኖ ለአምስት ዓመታት ያህል በዘረኝነትና የግል ጥቅምን ባለማስነካት በተፈጸመ ተንኰል ጉዳዩ ታፍኖ ከቈየ በኋላ ግና ከልጅነቱ የትዕግሥትን መራራነትና የፍሬዋን ጣፋጭነት ከሕይወት የተማረው ዓለማየሁ በአምስት ዓመት ከአራት ወር ውስጥ በ1950 ዓ.ም በጥር ወር ላይ የካፕቴንነት ማዕረግ አግኝቶ የአየር መንገዱ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ካፕቴን ለመሆን በቃ!

የኢትዮጵያ የንግድ አውሮፕላን የበረራ ታሪክን ጅማሬ እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር ከ1946 ዓ.ም. አንሥቶ አሥር ዓመታትን ብንቆጥር፣ በተከታታይ የምናገኘው የውጭ አገር አብራሪዎችን ስም ነው። የኢትዮጵያውያን ካፕቴኖችን ረድፍ በመምራት በቀዳሚነት





ስሙን ያስመዘገበው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ ወጣት የሠላሳ ሦስት ዓመቱ ካፕቴን ዓለማየሁ አበበ ሆነ። በዚሁ ማዕረግ የመጀመሪያው የካፕቴን ዓለማየሁ በረራ የተከናወነውም እንደ አውሮፓውያን አቈጣጠር በጥር 27 ቀን 1957 ዓ. ም. ነው።

ካፕቴን ዓለማየሁ በዳኮታ ዲሲ 3 ለአንድ ዓመት ተኩል በካፕቴንነት ካገለገለና በሂደቱም ብዙ ውጣ ውረዶችን ካሳለፈ በኋላ፣ ግንቦት 24 ቀን 1951 ዓ.ም የኮንቬየር 240 አውሮፕላን አብራሪ ሆነ። ከጥቂት ጊዜ በኋላም አየር መንገዱ በጊዜው ያስመጣውን ባለ አራት ሞተር ዲሲ 6ቢ አይሮፕላን ማብረር የሚችልበትን የምስለ በረራ ትምህርት በስዊዘርላንድ አገር ተከታትሎ ከተመለሰ በኋላ የዲሲ 6ቢ አይሮፕላን ተጠባባቂ ካፕቴን ሆነ። አፄ ኃይለ ሥላሴ በታኅሣሥ ወር 1953 ዓ.ም ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ብራዚል ለጉብኝት ሲሄዱ አብሮ በተጠባባቂ ካፕቴንነት የሄደው ዓለማየሁ ሲመለስ የሙሉ ካፕቴንነት መዕረግ ተቀበለ።

አየር መንገዱ ከፒስተን አውሮፕላን ተነሥቶ ወደ ጄት አውሮፕላን ለመሸጋገር ሲበቃ፣ ከጄት ቴክኖሎጂ ጋር እንዲተዋወቁ ቅድሚያ የተሰጠው በአየር መንገዱ ውስጥ ለነበሩ አሜሪካውያን ካፕቴኖች ብቻ ነበር። ነገር ግን ጥቂት ኢትዮጵያውያን እንኳን ይህንን ዕድል እንዲያገኙ ቦርዱ የአየር መንገዱን አስተዳደር በመወትወቱ፣ ካፕቴን ዓለማየሁ የጄት ካፕቴንነት ሥልጠና እድል አግኝቶ አሜሪካን አገር ወደሚገኘው ሲያትል ቦይንግ ፋብሪካ ከሌሎች ሠልጣኝ አሜሪካኖች ጋር ተላከ። በአየር መንገዱ ከተቀጠረ ጊዜ አንሥቶ ሲገረምመው የነበረው ጥቍሮችን ወደ ታች የማየት ንቀት አብረውት በሄዱት አሜሪካውያን ተከትሎት እዚያ በመድረሱ፣ የሥልጠናውን ደረጃ ዝቅ ለማድረግ ብዙ ጥልፍልፍ ሤራዎችን አቀዱበት። ትእግሥት ሞግዚት ሆና ያሳደገችው ወጣቱ ካፕቴን ዓለማየሁ ይህንን ሁሉ በእርጋታና በጥበብ እያለፈ፣ በዚያም የሚሰጠውን ሥልጠና ካጠናቀቀ በኋላ አየር መንገዱ የገዛቸውን ሁለት



አዱዲስ አውሮፕላኖች ከሌሎች ሰዎች ጋር በመከፋፈል እያበረረ ታኅሣሥ 3 ቀን 1962 ዓ.ም አዲስ አበባ ሲደርስ ለቡድኑ ደማቅ አቀባበል ተደረገለት።

ብዙም ሳይቄይ በሰሜን ምዕራብ አሜሪካ ሲያትል በሚገኘውና የአየር መንገዱ ደንበኛ በሆነው ቦይንግ ፋብሪካ የተሠራውን ሦስተኛውን ጄት በካፕቴን ዓለማየሁ ዋና አብራሪነትና በሌሎች ረዳት ኢትዮጵያውያን አብራሪዎች (ካፒቴን ደስታ ኀይሌና ካፒቴን ሀብቴ ተሰፋ ሚካኤል) አማካኝነት ይዘው መጡ። ይህ ዜና ከኢትዮጵያ አልፎ በአህጉራችን አፍሪካ ከማስተጋባቱም በላይ፣ በአሜሪካና በአውሮፓ በታወቁ ጋዜጦችም ላይ፣ "ኢትዮጵያውያን ፓይለቶች አዲሱን ጄት እያበረሩ ከአሜሪካ አዲስ አበባ ገቡ" በሚል ርእስ ዜናነት ቀረበ። "ካፕቴን ዓለማየሁ እንከን የማይወጣለት ብቁ ባለ ሙያና አፍሪካውያን ስላላቸው የቴክኒክ ብቃት ለማወቅና ለማረጋገጥ ለሚፈልጉ ሁሉ ሕያው ምስክር ነው። አየር መንገዱም በዓለማችን ካሉ እጅግ ውድ ዋጋ ካላቸው ጥቂት ባለ አውሮፕላን አየር መንገዶች አንዱ ነው።" በማለት የአሜሪካ ጋዜጦች ዘገቡ። ወቅቱ አብዛኛዎቹ የአፍሪካ አገሮች ከቅኝ ገዢዎች ቀንበር ነጻ ለመውጣት የሚታገሉበት ወቅት ስለ ነበር፣ ጥቁር ፓይለት በሚያበረው ዘመናዊ ጄት መሳፈር እንኳን በባዕዳን በወገኖቻችንም ዘንድ ቢሆን መደናገጥን ፈጥሮ እንደ ነበር የካፕቴን ዓለማየሁ የእስካሁን ድረስ ትዝታ ነው።

ኢትዮጵያውያን የአብራሪነት ችሎታቸውን በዓለም ዐቀፍ ደረጃ እያስመሰከሩ ሲመጡ በኢትዮጵያ አየር መንገድ መሥሪያ ቤት የአሜሪካኖቹ ብቸኛ ክልል ሆኖ የቀረው አስተዳደሩ ነበር። "አብራሪነቱን እንደ ምንም ብለው ቢደርሱብንም፣ በአስተዳደሩ ወንበር ላይ ለመቀመጥ የሃያ አምስት ዓመት ረጅም ጉዞ ይወስድባቸዋልና አያሠጋንም" ብለው ተቀምጠው ባሉበት ሁኔታ በከፍተኛ ውጣ ውረድና እልህ አስጨራሽ ጉዞ ካፕቴን ዓለማየሁ በየደረጃው ችሎታቸውን እያስመሰከሩ መጥተው ለአመራር ብቃት የቦርዱን እምነትና ድጋፍ አገኙ። ከዚህም የተነሣ በኢትዮጵያ አየር





መንገድ የዓለም ዐቀፍ በረራ ተጠሪ ዲሬክተር ሆነው ተሾሙ። ከዚያም በዋናነት ሲሠሩ የነበሩትን አሜሪካውያን ተክተው በዋና ዲሬክተርነት ማገልገል ጀመሩ፣ ለበለጠ ኀላፊነት ብቁ እንዲሆኑ ተብሎ እ.ኤ.አ በ1971 ዓ.ም. ከፍተኛ የአስተዳደር ትምህርት እንዲከታተሉ፣ ወደ አሜሪካ ስታንፎርድ ዩኒቨርስቲ ተላኩ። ከዚያም መልስ ካፕቴን ዓለማየሁ የበረራ ስምሪት ክፍል ኀላፊነትን ተረከቡ። በአጠቃላይ አየር መንገዱ ከተቋቋመ ከሃያ ስድስት ዓመት ትግል በኋላ ኢትዮጵያውያን የአስተዳደር፣ የጥገናና የበረራ ኃላፊነትን ሙሉ በሙሉ በመረከባቸው ኢትዮጵያውያኑ የአሜሪካውያኑን የጊዜ ግምት በአሥራ አምስት ዓመት አሳጥረውታል።

ከተወሰነ ጊዜ አገልግሎት በኋላ በኢትዮጵያ አየር መንገድ ከነበረው ያልተመቻቸ አሠራር የተነሣና በተጨማሪም ማስተማር በመፈለጋቸው፣ ካፕቴን ዓለማየሁ ዓልያምዳ በተባለው የየመን ዲሞክራቲክ አየር መንገድ የበረራውን ክፍል በኀላፊነት እንዲያስተዳድሩ ተቀጥረው ለሁለት ዓመታት አገለገሉ። ካፕቴን ዓለማየሁ በኢትዮጵያ አየር ኀይል ለሰባት ዓመት፣ ከዚያም በኢትዮጵያ አየር መንገድ ለሠላሳ አንድ ዓመት ካገለገሉ በኋላ የተራዘመ የጡረታ ጊዜያቸውን አገባደው በጡረታ ተሰናበቱ ። ነገር ግን ጡረታ በወጡበት ሰሞን ለኡጋንዳ አየር መንገድ ያቀረቡት የሥራ መጠየቂያ ተቀባይነት በማግኘቱ የቅጥር ውል ከኡጋንዳ አየር መንገድ ጋር ፈጽመው፣ የኡጋንዳን አየር መንገድ አብራሪዎች በማሠልጠን ለ3 ዓመት አገልግለው አየር መንገዱን ራሱን እንዲችል አድርገዋል ።

እንደ ሥራ ሕይወታቸው ሁሉ የካፕቴን ዓለማየሁ የትዳር ሕይወትም ትግልና ውጣ ውረድ የበዛበት ነበር ማለት ይቻላል። አየር መንገድ ሥራ በጀመሩ በአጭር ጊዜያት ውስጥ በዓለም ዐቀፍ አገልግሎት ጅቡቲና ኤደን ደርሶ መልስ ሲያገለግሉ፣ ትዳር የመያዝ አጋጣሚ ተፈጥሮ እናታቸው ግሪካዊት አባታቸው ደግሞ ኢትዮጵያዊ ከሆኑት ከፓሊን በላቸው ጋር ትዳር መሥርተው የመጀመሪያ



ልጃቸውን ሊሊያን የምስራች አለማየሁን ወለዱ። በመሀሉ በሥራ ሁኔታና በሌሎች ምክንያቶች መግባባት በመጥፋቱ ይህ ትዳር ሳይዘልቅ ቀርቶ ወደ በፊቱ የብቸኝነት ሕይወት ተመለሱ። በዚያ ሁኔታ ለጥቂት ዓመታት እንደ ቆዩ ሌላ አጋጣሚ ተፈጥሮ በንግድ ሥራ የተሰማሩና በቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ በጎ አድራጎት ድርጅት ዋና ሥራ አስኪያጅ በኋላም በዲፕሎማቲክ አገልግሎት ከታወቁት የአቶ ተፈሪ ሻረው ባለቤት እኅት ከሆኑት ከሚሚ ተስፋዬ ጋር ግንኙነት መሠረቱ። ከጊዜ በኋላ በንጉሡ ዘመን ከነበረው የእነ መንግሥቱ ነዋይ የመንግሥት ግልበጣ ግርግር ጋር ተያይዞ መላው የአቶ ተፈሪ ሻረው ቤተ ሰብ አባላት ወደ ስዊድን ሄደው መመለስ ባለመቻላቸው፣ ትዳሩ ሊዘልቅ ባይችልም ዮዲትንና ዳሽንን ወለዱ። ዮዲትና ዳሽን ከእናታቸው ጋር በስዊድን አገር ነዋሪ የነበሩ ሲሆን ዮዲት ባሁኑ ወቅት በተባበሩት መንግሥታት መሥሪያ ቤት በኒውዮርክ በኃላፊነት ቦታ በመሥራት ላይ ስትገኝ፣ ወንድ ልጃቸው ዳሽን በአሳዛኝ ሁኔታ በሃያ ዓመት ዕድሜው ስዊድን ስቶክሆልም አካባቢ በሚገኝ አንድ ሐይቅ ውስጥ ባልታወቀ ምክንያት ሰምጦ ሕይወቱ አልፏል ።

ከዚህ ሁሉ በኋላ በአሁኑ ወቅት አብረዋቸው በትዳር ካሉትና በእናታቸው ኢትዮጵያዊትና በአባታቸው ግሪካዊት ከሆኑት ከወ/ሮ ኤሊፍቴሪያ ዴሊስ ጋር በአስተናጋጅነት (ሆስተስነት ) በሚያገለግሉበት ጊዜ ተዋውቀውና ትዳር መሥርተው ግሩም፣ ሠላማዊት እና ብርሃን ዓለማየሁን ወልደው በደስታና በሰላም ኑሮአቸውን በመምራት ላይ ይገኛሉ። ካፕቴን ዓለማየሁ ባሁኑ ሰዓት በጥሩ አቋምና ጤንነት ላይ የሚገኙ ሲሆን፣ ይህንኑም ለመጠበቅ መጠነኛ የሆኑ የአካል እንቅስቃሴዎችን በየእዕቱ ያደርጋሉ። "ካፒቴን ዓለማየሁ በሙያቸው ምሣሌነትና ብቃት የታየባቸው በከፍተኛ የሥራ ጥረትና ሥነ ምግባር ጭምር መሆኑን አብሯቸው በጡረታ እስከተገለሉበት እስከ ታኅሣሥ 30 ቀን 1974 ዓ.ም ሁሉ የሚመሰክረው ነው።" ሲሉ የሥራ ባልደረባቸው የነበሩት ካፕቴን መኰንን በሪ "አብየሽን በኢትዮጵያ" በሚለው መጽሐፋቸው ገልጸዋል።





## መወድስ

ጽናትን ተምሮ ከትእግሥት ሞግዚቱ
ታተረ እንደ ጉንዳን በወጣትነቱ
ህልሙን እውን ሊያደርግ ተግቶ በመሥራቱ
በረረ እንደ ንስር በጎልማሳነቱ

## ትምህርተ ውልብታ

ምንም እንኳ የሕይወት ውጣ ውረድ ቢበዛብን በትእግሥትና በጽናት ካለፍነው ወደ ግባችን አቅጣጫ ያደርሰናል እንጂ አያወጣንም

ለራሳችን ያለን ግምት ለሕይወታችንና ለሙያችን ስኬት ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋል



## የውልብታ ምንጭ

አለማየሁ አበበ (ካፕቴን)1997 *ህይወቴ በምድርና በአየር*

መኮንን በሪ ( ካፕቴን ) 1995 *አቪየሽን በኢትዮጵያ*

<u>Ethio air star</u> ,1996 No-2 Golden Jubilee issue

Alpha-Ethiopia, sky lions(1996)airline pilots association

The Kansas city star July,19 1964

International Newsletter May 1986





## የአንባቢው የግል ማስታወሻ

